## ምዕራፍ 3

# ዳዊት

በመሳፍንት ዘመን የእስራኤል ሕዝብ «እንደ አሕዛብ ሁሉ የሚፈርድልን ንጉሥ አድርግልን» (1ሳሙ 8:5) ሲሉ ሳሙኤልን ጠየቁት:: በዚህ ጥያቄያቸው «በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁም...» (8:7) በማለት የጠየቁት እንዲደርግላቸው እግዚአብሔር ለሳሙኤል ተናገረው::

የእስራኤል ሕዝብ በንጉሥ እንዲመራ የእግዚአብሔር የቀደመ ሀሳቡ ነው:: ንጉሡም ከይሁዳ ወገን እንደሚሆን ቀደም ሲል «በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም...» (ዘፍ 49:10) በማለት ተናግሯል:: ሆኖም እግዚአብሔር የፈቀደው ሰውና ያሰበው ጊዜ እስኪመጣ ድረስ እስራኤላውያን መጠበቅ አልቻሉም:: ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ቃል ኪዳን ጸንቶ ከመቆየት ይልቅ «እንደ አሕዛብ ሁሉ እንሆናለን» (8:20) በማለት ንጉሥ ፈለጉ:: ይህ የሆነው ከይሁዳ ነገድ የሆነው ዳዊት ከመወለዱ ከአሥር ዓመት በፊት ነበር::

በእስራኤል መጀመሪያ ንጉሥ ሆኖ የተመረጠው ሳኦል ከብንያም ወገን ነው:: ሳኦል «ከእስራኤልም ልጆች ከእርሱ ይልቅ መልካም የሆነ ሰው አልነበረም፤ ከሕዝቡም ሁሉ ይልቅ ከትከሻውና ከዚያም በላይ ቁመቱ ዘለግ ያለ ነበረ» (1ሳሙ 9:2):: ይህ ውበቱና ቁመቱ (ካሪዝማ) በሳኦል መንፈሳዊ አመራር ላይ አልታየም:: ሳሙኤል እንኳን ንጉሥነት በውበትና በቁመት መስሎት «ወደ ኤልያብ





ተመልክቶ በእውነት እግዚአብሔር የሚቀባው በፊቱ ነው» ባለ ጊዜ «እግዚአብሔር ግን ሳሙኤልን፤ ፊቱን የቁመቱንም ዘለግታ አትይ፤ ሰው እንዲያይ እግዚአብሔር አያይምና ናቅሁት፤ ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል አለው» (1ሳሙ 16:6-7)። እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ እንደ ልቡ የሆነውን ዳዊትን መረጠ:: ዳዊት በዘይት ሲቀባ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ በኃይል መጣ (16:13)::

የእሴይ ስምንተኛ ልጅ የሆነው ዳዊት በወጣትነቱ የአባቱን በጎች ይጠብቅ ነበር (1ሳሙ 16:10-11፤17:12-14):: ዳዊት በብዙ ድፍረት አንበሳንና ድብን የገደለ፤ በእግዚአብሔር የታመነ ሰው ነበር (16:18፤ 17:38):: እግዚአብሔር ያዘዘውን ባለመፈጸሙ ምክንያት ሳዖልን ከንጉሥነቱ በናቀው ጊዜ ከእሴይ ልጆች መካከል ዳዊትን እንዲቀባ ነቢዩ ሳሙኤልን ላከው::

ዳዊት በገና በመደርደር ታላቅ ስጦታ ነበረው:: ንጉሡ ሳዖል በክፉ መንፈስ በተሰቃየ ጊዜ በዝማሬ እረፍትን ይሰጠው ዘንድ ወደ ቤተ መንግሥት የተጠራ ብላቴና ነበር:: ዳዊት በሳዖል ፊት ለጥቂት ጊዜያት ከቆየ በኋላ ወደ አባቱ ወደ ቤተ ልሔም ተመለሰ::

ፍልስጥኤማዊው ጎልያድ እስራኤልን ሊወጋ በወጣበት ወቅት አባቱ እሴይ ከሳዖል ጋር የነበሩትን የወንድሞቹን ሁኔታ እንዲጠይቅ ዳዊትን ልኮት ነበር:: ዳዊት የጎልያድን ሁኔታ ሲመለከት ልቡ ተነሳሣ:: ጎልያድንም በመግጠም የእግዚአብሔርን ስም ለማስከበር ሰልፍ ለመውጣት ወሰነ:: ዳዊት ጎልያድን በገጠመበት ጊዜ እድሜው ከሀያ ዓመት እንደሚያንስ ይገመታል::

በግ ጠባቂው ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም ወደ ሰልፍ የወጣው በእግዚአብሔር በአምላኩ ስም ወንጭፍና ጠጠር ይዞ ነው:: ጎልያድንም ግንባሩን መትቶ ጣለው፤ ድልም ለእስራኤል ሆነ::

ከድሉ በኋላ ሴቶች «ሳኦል ሺህ ገደለ ዳዊት እልፍ ገደለ» እያሉ በማዜማቸው ሳኦል በዳዊት ቀናበት፤ ጠላውም:: ስለዚህ እስከ ሞት ድረስ አሳደደው:: የዳዊት ዝና በእስራኤል እየወጣ ሲሄድ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ያለ ማቋረጥ ጥረት አደረገ:: በዚህ የማሳደድ ሁኔታ ውስጥ ዳዊት ሳኦልን ሊገድለው በሚችልበት ሁኔታ እንኳ አግኝቶት እግዚአብሔርን በመፍራት ሳይገድለው ቀረ (1ሳሙ 24:6-7)::

ከብዙ ዓመታት ስደት በኋላ ዳዊት በሰላሳ ዓመቱ በይሁዳ ኬብሮን ንጉሥ ሆኖ ተሾመ:: ከሰባት ዓመት በኋላ ደግሞ የእስራኤል ሁሉ ንጉሥ ሆነ:: ኢየሩሳሌምንም ዋና ከተማው አደረገ::

ዳዊት ንጉሥ ከሆነ በኋላ የወሰደው የመጀመሪያ ትልቅ ተግባር የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ከነበረበት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ ማድረግ ነበር (1ሳሙ 6):: ሊያመጣው ሲነሣ እንደ እግዚአብሔር ቃል ባለማድረጋቸው (ዘኁ 4) በሬዎቹ በፋነኑ ጊዜ ዖዛ እጆቹን ዘረጋ በዚያም የዖዛ ስብራት ሆነ (ዜና 13:9-12):: ዳዊት እንደገና በቂ ዝግጅት አድርጎ ወደ አዘጋጀው ድንኳን አመጣው::

በዳዊት ሕይወት ጨለማ የሆኑ ጊዜያት ነበሩ:: አንዱ ቤርሳቤህን በመውሰድ ኃጢአትን መፈጸሙ ነው:: ከዚያ አንዱን ኃጢአት ለመሸፈን ሲሞክር ሌላ ኃጢአት ውስጥ ገባ:: ባሏን ኦርዮንን አስገደለው:: እግዚአብሔር በነቢዩ ናታን በኩል ስለ ኃጢአተኝነቱ በተናገረው ጊዜ ግን ወዲያው ንስሐ ገባ:: የዚህ ኃጢአት ውጤት ግን በቀሪው ዘመኑ በብዙ መንገድ ተገለጠ:: በቤቱ ውስጥ የሰላም መጉደል፤ የልጆቹ መጠፋፋት፤ እርሱንም ከመንግሥት ለመፈንቀል መሞከር የኃጢአቱ ውጤት ነበረ::





ዳዊት በንጉሥነት ዘመኑ ሊያከናውን ከተመኛቸው ታላላቅ ሥራዎች አንዱ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ መሥራት ነበረ:: ይህንን ፍላጎቱን ለነቢዩ ናታን በነገረው ጊዜ የናታን መልስ «ሂድ አድርግ» ብሎ የሚያደፋፍር ነበር:: ናታን ነቢይ ቢሆንም እርሱም ሰው ስለሆነ እንደ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት መልካም መሆኑን በማሰብ አደፋፈረው:: በእርግጥ የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ምን ያዘገያል? ለመሆኑስ ጥያቄ የሚያስፈልገው ነገር ነው ወይ? ያሰኛል:: ይሁን እንጂ እግዚአብሔር «አንተ አትሠራልኝም» ብሎ የሚሠራለት ልጁ ሰሎሞን እንደሚሆን በናታን በኩል ለዳዊት ነገረው (2ሳሙ 7:1-17):: ዳዊትም እንደ ተባለው አደረገ::

ዳዊት ለአርባ ዓመት ያህል ከነገሠ በኋላ በሰባ ዓመቱ ሞተ (2ሳሙ 5:4):: በእግዚአብሔር ፊት ትሑት የነበረ ሰው (1ሳሙ 24:7፤ 26:11፤ 2ሳሙ 16:11፤ 19:22-23)፤ እስራኤልን ለድል የመራ መሪ፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመልካም ያስተዳደረ ንጉሥ ነበር (2ሳሙ 8:15፤ 1ዜና 18:14)::

ከዳዊት ሕይወትና አመራር በርካታ ጠቃሚ የመሪነት ትምህርቶችን እናገኛለን:: ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንመለከታለን::

### 1. ዳዊት:- ጦርነት የሚዋጋው ለእግዚአብሔር ስም ክብር ነበር::

ዳዊት የእግዚአብሔርን ጦርነት የሚዋጋበት ዋናው ምክንያት ለእግዚአብሔር ስም ክብር ሲል ነበር:: ይህም የመሪነትን ቦታ ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ቦታውን ለምን ዓላማ እንደሚፈልገው እንደ ታላቅ መለኪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል::

ጎልያድ በየቀኑ እየወጣ ለአርባ ቀን ሙሉ ይንጎራደድ በነበረበት ጊዜ የሳዖል ተከታዮች ልብ ይቀልጥ ነበር፡፡ ጎልያድ እስራኤልን ወክሎ እርሱን የሚገጥም «አንድ ሰው ስጡኝ» (1ሳሙ 17፡10) እያለ ሲጠይቅ በጊዜው እስራኤልን የሚወክል አንድ ጀግና ግን አልተገኘም፡፡ በአምላኩ ከታመነ ከዳዊት በስተቀር ሌላው ሕዝብ ሁሉ «እጅግ ፈሩ፤ ደነገጡም» (17፡11)፡፡

ከፍልስጥኤማውያን የሚወጣው ጎልያድ ፍልስጥኤምን ይወክላል፤ ከእስራኤል የሚወጣው ያ አንድ ሰው (ወጣት) ዳዊት ደግሞ እስራኤልን ይወክላል፡፡ ያ አንድ ሰው ከሞት ከዳነ ሌሎችን ሁሉ የሚያድን (የሚታደግ) ይሆናል፡፡ ከተሸነፈ ደግሞ ለእስራኤል ሽንፈትን የሚያመጣው ተወካዩ ነው፡፡ እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ ሰው ይፈልጋል፡፡ ሀሳቡን ከሚያገለግልና የሚያደርገውን ሁሉ ለእርሱ ክብር ከሚያደርግ ከአንድ ሰው ጋር ታላቅ ነገርን ይሠራል፡፡

ዳዊት «ይህን ፍልስጥኤማዊ ለሚገድል፤ ከእስራኤልም ተግዳሮት ለሚያርቅ ሰው ምን ይደረግለታል? የሕያውን አምላክ ጭፍሮች የሚገዳደር ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን ነው?» (1ሳሙ 17፡26) በማለት ጠየቀ፡፡ ሕዝቡም ከሳኦል የተሰጠውን ተስፋ ጎልያድን «የሚገድለውንም ሰው ንጉሥ እጅግ ባለጠጋ ያደርገዋል፤ ልጁንም ይድርለታል፤ ያባቱንም ቤተ ሰብ በእስራኤል ዘንድ ከግብር ነጻ ያወጣቸዋል» (17፡25) አሉት፡፡ ሳዖል ጎልያድን ለሚገድል ሰው ሊሰጠው ያሰበው ከንጉሥ የመጣ ትልቅ ስጦታ ነው፡፡ እንደ ሽልማት እንዲሆን የታሰበው ይህ የኑሮ መሻሻልና ከንጉሥ ጋር መወዳጀት ዳዊትን አላጓጓውም፡፡

የዳዊት የሕይወት ዓላማ ከሀብትና ከመዛመድ በላይ ነው፡፡ የጎልያድ ሁኔታ ዳዊትን የከነከነው የሕያው እግዚአብሔርን የቃል ኪዳን ሕዝብ የሚገዳደር (ለማዋረድ የተነሣ) ሰው መሆኑ ነው፡፡ ዳዊት ውርደትን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ለማራቅ ወደ ጦርነት ገባ፡፡





ለፍልስጥኤማውያን የኃይልና የድል ምንጫቸው ጣዖቶቻቸው ናቸው፡፡ የሚዋጉት በጣዖቶቻቸው ስም ነው፡፡ «ፍልስጥኤማዊውም [ጎልያድ] በአምላኮቹ ስም ዳዊትን ረገመው» (17፡43)፡፡ ዳዊት ደግሞ ጦርነት የሚዋጋው በእግዚአብሔር ስም ነው፡፡ «ዳዊት ፍልስጥኤማዊውን አለው፡- አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን ዛሬ በተገዳደርኸው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ» (1ሳሙ 17፡45-46)፡፡ ይህም በመሆኑ «ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው» (17፡47) እንጂ የዳዊት ወይም የሳዖል አልነበረም፡፡

ሰልፉ የእግዚአብሔር መሆኑን ያወቀ ሰው ለራሱ መመቻቸት አይሠራም፤ ራሱን አያከብርም፤ በመጨረሻም ራሱን «ድል አድራጊ» አድርጎ አያቀርብም፡፡ የሚያደርገውን ሁሉ በእግዚአብሔር ስምና ለእርሱም ክብር ያደርገዋል፡፡ ዳዊት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል፡፡

ጎልያድ ለጦርነት የተዘጋጀና በደንብ የታጠቀ ሰው ነበር፡፡ ዳዊት ደግሞ ከወንጭፍና ከድንጋይ ሌላ ምንም አልያዘም፡፡ ተዋጊው እግዚአብሔር ባልተለመደ መሣሪያ ለደካማው ድልን ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው እንደ ዳዊት በእርሱ የሚታመንን ሰው ነው፡፡ በጩኸት እያሪኮ እንደ ፈረሰ እናውቃለን (ኢያ 6፡5)፡፡ መዘምራንም በጦርነት በሰልፍ ፊት ቆመው እንዲዘምሩ ታዘዋል፤ ድልም ለእስራኤል ሆኖአል (2ዜና 20፡22)፡፡ ጌዲዎን በችቦ ድል አድርጎአል (መሳ 7፡16-18)፡፡ ሐማ ባዘጋጀው መስቀያ ተሰቀለ (አስ 7፡10)፤ ምድያማውያን በእጃቸው መሣሪያ እርስ በርስ ተጠፋፉ (መሳ 7፡22)፤ ጎልያድ በራሱ ሰይፍ ተገደለ፡፡

የብንያም ወገኖች በወንጭፍ «አንዲት ጠጉርስ እንኳ አይስቱም» (መሳ 20፡16) ተብሎ የተመሰከረላቸው ነበሩ፡፡ ሳኦል ከብንያም ወገን በመሆኑ በወንጭፍ ጎልያድን መትቶ ለመጣል ራሱ ወይም

ከብንያም ወገን የሆነ ሌላ ሰው በተገኘ ነበር:: ቁም ነገሩ በእግዚአብሔር መታመንና ለእርሱም ክብር መዋጋት በመሆኑ ዳዊት ሌሎች በጣም በሰለጠኑበት መሣሪያ ተጠቅሞ የእስራኤልን ተግዳሮት አስወገደ::

ዳዊት ጦርነትን የሚዋጋበት ዋና ምክንያት «...ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ ታውቅ ዘንድ ይህም ጉባኤ ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደለ ያውቅ ዘንድ ነው» (1ሳሙ 17:46-47) ይላል:: ስለዚህ እግዚአብሔር መከናወንን የሚሰጠን ለምንድን ነው? እርሱ አምላክ እንደሆነ እንዲታወቅ ነው:: ነቢዩ ኤልያስ ከበዓል ነቢያት ጋር በነበረው ክርክር መሥዋዕቱን ሲያቀርብ የጸለየው «አቤቱ:- የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፤ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደሆንህ፤ እኔም ባሪያህ እንደሆንሁ፤ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ» (1ነገ 18:36) እንዳለው ነው:: እንደ ዳዊት ሁሉ የኤልያስም ጥረት በእስራኤል ላይ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ በሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግ ነው::

ንጉሡ ሕዝቅያስም ከአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ስለመጣበት ተግዳሮት ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ «እንግዲህ አምላካችን አቤቱ፤ የምድር መንግሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ እንድታድነን እለምንሃለሁ» (2ነገ 19:19) አለ:: እንዲሁ የቀደሙት ነቢያትና ሐዋርያት አገልግሎታቸውም እግዚአብሔርን ለሰው ሁሉ መግለጥ (ማሳወቅ) እና ሁሉን ለእርሱ ክብር ማድረግ ነበር::

እኛም ዛሬ እግዚአብሔር በእጃችን ታላላቅ ሥራዎችን ቢሠራ፤ ታአምራትንም ቢያደርግ ይህን የሚያደርገው እርሱ ሕያው አምላክ ስለሆነ ነው:: እንደ ዳዊት የእግዚአብሔርን አምላክነት ለምድር





ሁሉ ማሳወቅ የእኛ የአገልግሎታችን ድርሻ ነው:: የምናገለግለውም ለስሙ ክብር ሊሆን ይገባል::

## 2. ዳዊት:- የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የተወጣ ሰው::

ዳዊት በብላቴንነት ዕድሜው አባቱ እሴይ ወደ ወንድሞቹ በላከው ጊዜ መልእክቱን ለማድረስ ሲሄድ የሚጠብቃቸውን በጎች የትም ጥሎ አልሄደም፤ «በጎቹንም ለጠባቂ ተወ» (1ሳሙ 17:20):: ዳዊት ገና ከብላቴንነቱ ጀምሮ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የሚወጣ ሰው ነበር::

ዳዊት የአባቱን ትእዛዝ ለማድረስ ወደ ወንድሞቹ በቀረበ ጊዜ የወንድሙ «የኤልያብ ቁጣ በዳዊት ላይ ነድዶ:- ...እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኩራትህን የልብህን ክፋት አውቃለሁና» (17:28) በማለት ተናገረው:: ኤልያብ በእድሜ ታላቅ የሆነና ነገሮችን ጠንቅቆ የሚያውቅ ቢመስለውም በዳዊት ልብ ውስጥ የነበረውን ቅንነትና ለእግዚአብሔር ስም የነበረውን ቅንዓት አልተረዳም:: ኤልያብ ዳዊትን የሚከሰው ኩራትና የልብ ክፋት አለብህ ብሎ ነው፤ ዳዊት ደግሞ ወደ ሰልፍ የወጣው ያ «ታላቅ ነገር» (17:29) ስለሆነ ነው:: ታላቅነቱም እስራኤልን የሚገዳደር እያለ ለእግዚአብሔር ስም የሚቀና ሰው ዝም ብሎ መቀመጥ አለመቻሉ ነው::

ዳዊት ለበጎቹ እንዳደረገ ሁሉ በሌላም ሁኔታ ሰልፉን ሊያይ ሲወጣ «...ዕቃውን በዕቃ ጠባቂው እጅ አኖረው» (17:22):: ዳዊት መጀመሪያም በጎቹን ለጠባቂ ሰጥቶ ሄደ፤ በኋላም ዕቃውን በጠባቂ እጅ አኖረው:: እንዲሁም በሳኦል ተሰድዶ አገር ጥሎ ሲሄድ ለአባቱና ለእናቱ ተጠነቀቀ:: «ዳዊትም ከዚያ በሞዓብ ምድር ወዳለችው ወደ ምጽጳ ሄደ፤ የሞዓብንም ንጉሥ:- እግዚአብሔር የሚያደርግልኝን እስካውቅ ድረስ አባቴና እናቴ ከአንተ ጋር

ይቀመጡ ዘንድ አለምንሃለሁ አለው» (22:3):: ዳዊት ወላጆቹን አሳዳጁ ወደማይደርስባቸው ወደ ሞዓብ ምድር ወሰዳቸው:: የሞዓብ ምድር ሳኦል የማይሻገርበት የሌላ ሰው ምድር ነው:: ዳዊት የተሰጠውን ኃላፊነት ከትንሽ እስከ ትልቅ ይወጣል::

የእግዚአብሔር ቃል «ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሩአት፤ እነርሱ አስቀድመው ለገዛ ቤተ ሰዎቻቸው እግዚአብሔርን መምሰልን ያሳዩ ዘንድ፤ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ፤» (1ጢሞ 5:4) እንዲሁም «ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው (5:8) ይላል:: ወጣቱ ዳዊት ይህን ጠንቅቆ ያወቀና በችግሩ ጊዜ (ወቅቱ ቀውጢ ቢሆንም) ኃላፊነቱን በአግባቡ የተወጣ ሰው ነው::

እግዚአብሔር ዳዊትን ወደ ንጉሥነት ያነሣው ከበግ ጥበቃ ነው:: እንግዲህ ከዳዊት እንደምንማረው አንድ ሰው ወደ ሌላ ኃላፊነት ሲዛወር ወይም በሹመት ሲያድግ በእጁ ያለውን ሥራና ኃላፊነት በአግባቡ ለሌላው አስረክቦ መሄድ አለበት:: እግዚአብሔር በትንሹ የታመነን ሰው የሚያሳድግበት መንገድ አለው:: ትንሹን የናቀ ግን ትልቁንም አያየውም (ሉቃ 16:10):: እኛም የተሰጠንን በትክክል እናወራርድ::

## 3 ዳዊት:- በጽድቅ እየኖረ በእግዚአብሔር ጊዜ ንጉሥ ሆኖ የተሾመ ሰው::

ዳዊት ምንም እንኳን በእግዚአብሔር የተቀባና የንጉሥነት ስፍራው ለእርሱ የተሰጠው እንደሆነ ቢያውቅም የቀባው እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ብቻ ዙፋኑን ለመውሰድ የታገሠ ሰው ነው:: ይልቁንም አሳዳጁን ሳኦልን ሊገድለው ሲችል እግዚአብሔርን በመፍራቱ በሳኦል ላይ እጁን አላነሳም::





«የዳዊትም ሰዎች:- እነሆ፤ ጠላትህን በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፤ በዓይንህም ደስ የሚያሰኝህን ታደርግበታለህ ...ቀኑ ዛሬ ነው» (1ሳሙ 24:4) ባሉት ጊዜ ዳዊት «የሳኦልን መጎናጸፊያ ዘርፍ በቀስታ ቆረጠ» (24:5):: ይህንም ስላደረገ እንኳን «የዳዊት ልብ በኀዘን ተመታ ...እግዚአብሔር የቀባው ነውና» (24:5-6) አለ:: በዚህ ወቅት ዳዊት ሳኦልን ሊገድለው ምቹ ሁኔታ ነበር:: ግን እግዚአብሔርን የሚፈራና በብዙኀን ድምጽ የማይነዳ ዳዊት በፊቱ ጽድቅ የሆነውን ነገር ብቻ ለማድረግ ወሰነ:: በአደራረጉም ጻድቅ መሆኑን አሳዳጁ ሳኦል ሳይቀር «እኔ ክፉ በመለስሁልህ ፋንታ በጎ መልሰህልኛልና አንተ ከእኔ ይልቅ ጻድቅ ነህ» (24:17) በማለት መሰከረለት::

በሌላም ሁኔታ ምንም እንኳ ሳኦል በማሳደዱ ቢቀጥልም ሳኦልን ተኝቶ ሲያገኙትና ከዳዊት ጋር የነበረው ሰው «...እኔ በጦር አንድ ጊዜ ከምድር ጋር ላጣብቀው» (26:8) ባለው ጊዜ የዳዊት መልስ «እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንጹሕ አይደለምና አትግደለው አለው» (26:9):: እንዲሁም እግዚአብሔር ይመታዋል» (26:10) በማለት ፍርድን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ሰጠ::

የእግዚአብሔርን ተስፋ ተቀብሎ እስከሚፈጸም ድረስ ታላቅ ትዕግሥት ይጠይቃል:: ይልቁንም በእግዚአብሔር የተናቀ ሰው አሳድጅ ሆኖ ባለ ተስፋ የሆነ ሰው ተሳዳጅ ሲሆን የበለጠ ይፈትናል:: ሆኖም እግዚአብሔርን መፍራት አጋጣሚን ተጠቅሞ ወደ ሥልጣን አለመውጣትንና የእግዚአብሔርን ጊዜ መጠበቅን ያጠቃልላል:: ዳዊት አስቀድሞ የመረጠው ቦታውን እንዲሰጠው እግዚአብሔርን እንደ ጠበቀ ሁሉ በእጅ ላይ ደም እንዳይኖር በመጠንቀቅና የእግዚአብሔርን ጽድቅ አሠራርና መጠበቅ ታላቅ ማስተዋል ነው::

4. ዳዊት፡- የተሰበረ መንፈስ የነበረው፣ የቅንነት መለኪያ፡፡
ዳዊት እግዚአብሔርን የመውደዱንና ጠንካራ መሪ የመሆኑን ያህል ድካም የታየበትም ሰው ነው፡፡
ዳዊት የማመንዘር ኃጢአት የፈጸመና ሰውንም ያስገደለ ሰው ነው፡፡ የችግሩ መነሻ ነገሥታት ወደ ሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ እርሱም እንደ ንጉሥነቱ ወደ ሰልፍ መሄድ ሲገባው ታቦቱንና ሠራዊቱን ልኮ እርሱ በሰፈር መዋሉ ነበር (2ሳሙ 11፡1)፡፡ አንድ የተሳሳተ እርምጃ ቶሎ ካልተስተካከለ በስተቀር ወደ ሌላ ስህተት ያመራልና ዳዊት መልእክተኞችን ልኮ ስትታጠብ ያያትን ሴት ጠየቀ፣ ቤርሳቤህንም አስመጣት (11፡4-5)፡፡

መጽሐፍ «ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፣ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» (ያዕ 1፡14-15) እንደሚል በማየት የጀመረው ምኞት ኃጢአትን ወለደ፡፡ ቃሉ «እነሆ፣ እግዚአብሔርን ትበድላላችሁ ኃጢአታችሁም እንዲያገኛችሁ እወቁ» (ዘኁ 32፡23) እንደሚል ዳዊት በድብቅ የሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር በአደባባይ ገለጠው፡፡ ይህ ጊዜ ዳዊት በሕይወቱ ዝቅ ያለበት፣ ያፈረበትና የተዋረደበት ነበር፡፡

ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላና ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ መጥቶ «ያ ሰው አንተ ነህ» (2ሳሙ12፡7) ባለው ጊዜ የዳዊት መዝሙር (ጸሎት) «አቤቱ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፣ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ፡፡ ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፣ ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና፡፡ አንተን ብቻ በደልሁ፣ ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፣ በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ ...» (መዝ 51፡1-9) የሚል ንስሐና ልመና ነበር፡፡ ምሕረትንም ሲቀበል «የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም»





(መዝ 51፡17) ብሎ ነበር፡፡ ዳዊት የተሰበረ መንፈስ፣ የተዋረደ ልብ የነበረው ሰው ነው፡፡

እግዚአብሔር የዳዊትን ኃጢአት ይቅር ቢልም በድርጊቱ የእግዚአብሔር ስም ተሰድቧልና ስለዚህ ቅጣት እንደሚቀበል ናታን ለዳዊት ነገረው፡፡ «ናታንም ዳዊትን እግዚአብሔር ደግሞ ኃጢአትህን አርቆልሃል፣ አትሞትም። ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ ደግሞ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው»። ከዚያ በኋላ ዳዊት በጾምና በጸሎት ስለ ሕፃኑ እግዚአብሔርን ቢለምንም «እግዚአብሔርም የኦርዮ ሚስት ለዳዊት የወለደችውን ሕፃን ቀሠፈ» (2ሳሙ 12፡13-15)፡፡ የእግዚአብሔርን ስም ለሚያሰድብ ኃጢአት በንስሐ ይቅርታ መቀበል ቢቻልም ለበደሉ ግን ቅጣት መቀበል ሊኖር ይችላል ማለት ነው!!

በሌላም ሁኔታ ዳዊት ሕዝቡን በመቁጠሩ «የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ» (2ሳሙ 24፡1)፡፡ ሕዝብን መቁጠር በራሱ ስህተት አይደለም፡፡ ሙሴም የሚመራውን ሕዝብ ቁጥር ያውቅ ነበር፡፡ ስድስት መቶ ሺህ እግረኛ (ዘኁ 11፡21) እንደሚል፡፡ በራሱ ኃጢአት ያልሆነ ተግባር በሌላ ዓላማ ሲደረግ ግን በደል ሆኖ ሊቆጠር ይችላል፡፡

ዳዊት ሲቆጥር የሚቆጥረው የሰልፍ ኃይሉንና ጉልበቱን ለመለካት ስለፈለገ ነበር፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ያየው ዳዊት መቁጠር የፈለገበትን የውስጥ ፍላጎት (ዓላማ) ነው፡፡ ልብን የሚያውቅ እግዚአብሔር በዳዊት ድርጊት ተቆጣ፡፡ ከቆጠራቸውም ሰዎች መካከል እግዚአብሔር ቀነሰበት፡፡

ይህ ድርጊቱ በእግዚአብሔር ፊት በደል እንደሆነ ነቢዩ ጋድ ሲነግረው ዳዊት በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል፡፡ «እጅግ

በድያለሁ ...ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁና፤ የባሪያህን ኃጢአት ታስወግድ ዘንድ እለምንሃለሁ» (ዜና 21፡8) አለ። እግዚአብሔር የሚፈልገው ልብ እንደዚህ ዓይነቱን ነው።

ከዳዊት ልብ ጋር ለማነጻጸር አቤሴሎምንና አኪጦፌልን እንመልከት። የዳዊት ልጅ አቤሴሎም በረጅም ዘመን ድብቅ (ስውር) የግል ዓላማ የሕዝብን «ልብ የሰረቀ» ሰው ነበር። አቤሴሎም በማለዳ ተነስቶ በበሩ አደባባይ በመቆም ከንጉሥ ለማስፈረድ ጉዳይ ያለውን ሰው ሁሉ ወደ እርሱ እየመራ በሐሰት የደለለ ሰው ነበር። ሰው ሁሉ ወደ እርሱ ይመጣ ዘንድና «ቅንም ፍርድ እፈርድለት ዘንድ በአገር ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ? ይል ነበር። ሰውም እጅ ሊነሣው ወደ እርሱ በቀረበ ጊዜ እጁን ዘርግቶ ይይዝና ይስመው ነበር» (2ሳሙ 15፡4)። ይህን ለምንድነው የሚያደርገው? የእስራኤል ሰዎችን ልብ ለመስረቅ ነው (15፡6)።

አቤሴሎም የልቡን ሀሳብ ማንም ሳያውቅበት ወደ ንጉሥነት ለመምጣት ለረጅም ዓመታት ያሴረ ሰው ነው። ዓመቱንም ስንቆጥር አምኖን እህቱን ካስነወረ በኋላ ሁለት ዓመት ጠብቆና ግብዣ አዘጋጅቶ ወንድሙን ገደለ (13፡23-29)። ሦስት ዓመት ኮብልሎ በጌሹር ቆየ (13፡38)። ከዚያም ከአራት ዓመት በኋላ ወደ ኬብሮን ሄደ (15፡7-11)። እንግዲህ ዘጠኝ ዓመት መሆኑ ነው። ስለት ለማቅረብ በሚል ሰበብ ወደ ኬብሮን ሄዶ «ጽኑ ሴራ» (15፡12) አደረገ። እንዲህ ዓይነት ቅንነት የሌለበት መንገድ በእግዚአብሔር የተናቀ ነው።

ቃሉ «በክፉ ሥራ ላይ ፈጥኖ ፍርድ አይፈረድምና ስለዚህ በሰው ልጆች ውስጥ ልባቸው ክፉ ለመሥራት ጠነከረ» (መክ 8፡11) እንደሚል አቤሴሎም እግዚአብሔር በሰጠው ረጅም የንስሐ ዘመን አልተጠቀመበትም፤ በሴራው ቀጠለ መጨረሻውም የከፋ ሆነ (18፡9-14)።





አኪጦፌል የዳዊት የታወቀ መልካም መካሪ (አማካሪ) ነበረ (16፡23)። «በዚያም ወራት የመከራት የአኪጦፌል ምክር የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መጠየቅ ነበረች» (16፡23)። ነገር ግን አቤሴሎም አባቱን ዳዊትን ለማሳደድ ሲፈልግ አቤሴሎምን በክፉ የመከረው የዳዊት «የውስጥ አዋቂ» ይኸው አኪጦፌል ነበር (17፡1-4)። አኪጦፌል ተረኛው ንጉሥ አቤሴሎም እንደሚሆን ስለ ገመተ ፈጥኖ መወዳጀቱ ነበር። ቅንነት የሌለበት መንገድ ነው። አኪጦፌል ምክሩ እንዳልሠራለት ሲያይ «በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ» (17፡23)።

የሳኦልም ሁኔታ እንዲሁ ነበር። ሳኦል የወሰደው እርምጃ ልክ አለመሆኑን ሳሙኤል ሲነግረው የሰጠው መልስ «ሕዝቡን ፈራሁ ስለ ሕዝቡ ይህን አደረኩ...» (1ሳሙ 15) የሚል ነበር። ምክንያት ሰጠ እንጂ ንስሐ አልገባም ።

የተሰበረ መንፈስ ያለው ሰው ዳዊት ግን ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ እግዚአብሔር ሲናገረው ንስሐ ለመግባትና ከአምላኩ ጋር ያለውን ኅብረት ለማስተካከል ጊዜ አልወሰደበትም። ስለሆነም ከእርሱ በኋላ ለተነሡ ነገሥታት ሁሉ ስለ ቅንነቱና እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ ስለ መከተሉ መለኪያ ሆኗል። ሌሎቹ ነገሥታት ቅንነታቸው ወይም እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ መከተላቸው «እንደ ዳዊት» በሚል ይነጻጸሩና ይወዳደሩ ነበር። ለምሳሌም «እንደ ዳዊት እግዚአብሔርን በመከተል ፍጹም አልሆነም» (1ነገ 11፡6)፤ «አባቱም ዳዊት እንዳደረገ በፊቱ ቅን ነገር ያደርጉ ዘንድ» (11፡33)፤ «ልቡም እንደ አባቱ እንደ ዳዊት ልብ ከአምላኩ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም አልነበረም» (15፡3)፤ «እንደ አባቱ እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ» (15፡11) ተብለዋል።

እንግዲህ መሪዎችም ሰዎች ናቸውና ሊሳሳቱ ይችላሉ። እንዳይሳሳቱ እግዚአብሔርንም እንዳያሳዝኑ መጠንቀቅ አለባቸው።

እግዚአብሔርን በመፍራት መሄድ አለባቸው:: ሆኖም ከተሳሳቱ ኃጢአታቸውን በመደበቅ ወደ በለጠ ማጥ እንዳይገቡ ፈጥነው በንስሐ በመቅረብ ምሕረትን ከእግዚአብሔር መለመን ይገባቸዋል::

## 5. ዳዊት:- ለሰው ሁሉ ያለ አድልዎ መልካምን ያደረገ እረኛ::

መሪ በሥልጣን ላይ በመጣ ጊዜ ሥልጣኑን እግዚአብሔርን በመፍራት ካልተጠቀመ በስተቀር «የማይፈልጋቸውን» ለመበቀል ለሚያቀርባቸው ደግሞ ልዩ ጥቅም ለመስጠት መንገድ ይፈልጋል:: በአንዳንዶች ዘንድ ከፍተኛው የሥልጣን ቦታ የሚፈለገውም ለዚሁ ነው:: ዳዊት ግን ልዩ ሰው ነበር:: «ዳዊትም በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ፤ ዳዊትም ለሕዝቡ ሁሉ ፍርድንና ጽድቅን አደረገላቸው» (2ሳሙ 8:15፤ 1ዜና 18:14) እንደተባለ ለእያንዳንዱ የሚገባውን በማድረግ ያለ አድልዎ የመራ ሰው ነው::

የእግዚአብሔር ንብረቱ ሕዝቡ ነውና ለሕዝቡ ይጠነቀቃል:: እግዚአብሔር መሪዎች እርሱን እንዲፈሩትና በሕዝቡ ላይ በጽድቅ እንዲያስተዳድሩ ይወዳል (2ሳሙ 23:3):: የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች የሕዝቡ ጠባቂ እረኞች ናቸውና አንዱ ተግባራቸው ሰውን ሁሉ ያለአድልዎ ማስተዳደር ነው:: ዳዊት ስለ ሰሎሞን ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይም «አቤቱ፤ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፤ ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ፤ ሕዝብህን በጽድቅ፤ ችግረኞችህንም በፍርድ ይዳኝ ዘንድ» (መዝ 72:1-2) ብሏል:: ጽድቅና ፍርድ የእግዚአብሔርን ገዥነት (ልዕልና) የሚገልጹ ባሕርያት ናቸው:: «የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው» (መዝ 89:14) እንደሚል::

ከንጉሥ ኃላፊነት መካከል ሕዝብን መምራት፤ ከጠላት መጠበቅ (1ሳሙ 8:20)፤ እና በጽድቅ ማስተዳደር ዋናዎቹ ናቸው (ኢሳ





32:1፤ ኤር 23:5-6):: ዳዊት የእስራኤል ከፍተኛው ባለ ሥልጣን በመሆኑ ከባድ ጉዳዮች በእርሱ ይዳኙ ነበር (2ሳሙ 14:1-20):: የተቀሩት ጉዳዮች በየደረጃው ባሉ የተሾሙ አስተዳዳሪዎች ይዳኛሉ (2ዜና 19:5-7)::

የዳዊት አስተዳደር ሕዝቡን በእኩል ዓይን በማየት ነበር:: አንድ ጊዜ ከውጊያ መልስ ሰዎች «ካስጣልነው ምርኮ ምንም አንሰጣቸውም» (1ሳሙ 30:22) ብለው ለዳዊት ሲናገሩ «የተዋጉትና ዕቃውን የጠበቁት ዕድል ፈንታ እኩል ይሆናል» (1ሳሙ 30:24) ብሎ ዳዊት ፍርድ ሰጠ:: ይህ የጽድቅ ፍርድ ምሳሌ ነው::

መልካም አስተዳደር የሚኖረው ከላይ እስከ ታች የተዘረጋና የተያያዘ ጥሩ የአሠራር መዋቅርና የሥራ ዝርዝር ሲኖር እንዲሁም በመዋቅሩ ውስጥ ተገቢ ሰዎች ሲኖሩ ነው:: ዳዊት ለሕዝቡ ሁሉ ፍርድንና ጽድቅን ያደረገበት አንዱ መንገድ ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በማበጀትና ከእርሱ ሥር በጽድቅ የሚሠሩ ፍትሕን የሚወዱ ሰዎችን በመሾም ነበር:: ዳዊት ለሕዝቡ ሁሉ ጽድቅና ፍርድ ያደረገው በመንግሥት ሥራ (1ዜና 27)፤ እና ለጭፍሮችም (ጦር ሠራዊቱ) ሁሉ (1ዜና 28) ነበር::

እንግዲህ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያለው አመራር ሕዝብን ሁሉ በጽድቅ ለማስተዳደር እውነተኛ ሚዛንና እውነተኛ መለኪያን መጠቀም ሲኖር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መልካም አስተዳደር ለማስተማር ተብሎ የተጻፈ መጽሐፍ ባይሆንም ስለ ጥሩ ማኔጅመንት ትምህርት ይሰጣል:: መልካም አስተዳደር የሚመጣው እግዚአብሔርን በመፍራት ነው::

6. ዳዊት:- በእግዚአብሔር የተፈቀደለትን ሥራ ብቻ የሚሠራ አለቃ::

እግዚአብሔር በዳዊት ላይ ያደረገው ጸጋ ብዙ ነው:: የንጉሥነት ቅባት ነበረው፤ ዘማሪም ነበር:: ዳዊት ወደ መንግሥት ከመጣ በኋላ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አሰበ:: ለእግዚአብሔርም በመቅናት «ነቢዩ ናታንን፤ እኔ በዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ፤ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ አለው» (2ሳሙ 7:2)::

ዳዊት በሕይወት ዘመኑ ካደረገው መከናወን በላይ ቤተ መቅደሱን ቢሠራ ምናልባት እጅግ ደስተኛ በሆነ ነበረ:: ዳዊት ቤተ መቅደሱን መሥራት ማሰቡ መልካም እንደሆነ በማሰብ ነቢዩ ናታን «እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ሂድ፤ በልብህም ያለውን ሁሉ አድርግ አለው» (7:3):: ለነገሩማ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሥራት ምን ስህተት አለበት? የነቢዩ ናታን ምክር ግን ትክክል አልነበረም:: የታወቁ ነቢያትስ ቢሆኑ እግዚአብሔርን አድምጠው ካልተናገሩ ሰው ናቸው እኮ! ይሳሳታሉ:: ሆኖም የእግዚአብሔር ሀሳብ ቤቱን ዳዊት እንዲሠራለት አለመሆኑን ነቢዩ ናታን በተረዳ ጊዜ ይህንኑ «አንተ የምኖርበትን ቤት አትሠራልኝም» (7:6) ይልሃል እግዚአብሔር ብሎ ለዳዊት ነገረው::

እንዲሁም «ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ፤ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፤ መንግሥቱንም አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል...» (2ሳሙ 7:12-13) ብሎ ተናገረው:: ይህ የተባለለት ሰሎሞን ግን ገና አልተወለደም ነበር:: ዳዊት ለቤተ መቅደሱ ምሳሌ የተቀበለ፤ ለመሥራትም የፈለገ ቢሆንም «እኔ ለአምላኬ ለእግዚአብሔር ቤት እሠራ ዘንድ በልቤ አስቤ ነበር:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ:- ...ለስሜ ቤት አትሠራም» (1ዜና 22:7-8) አለኝ በማለት ለቃሉ ታዘዘ እንጂ አልተገዳደረም፤ በአምቢተኝነት ለመቀጠልም አልሞከረም::





ዳዊት ቤተ መቅደሱን መሥራት ባይፈቀድለትም መደረግ የሚገባውን ዝግጅት ሁሉ አደረገ ለሥራው «ብዙ አዘጋጀ» (22:5):: ለልጁም ለሰሎሞን ሥራውን ከነምሳሌው ሰጠው:: እንዲሁም «ሰሎሞንን ጠርቶ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ይሠራ ዘንድ አዘዘው» (22:6):: አስፈላጊውን ዕቃ በመሰብሰብ (2ዜና 28:2፤ 29:1-2)፤ የራሱንም መዋጮ አድርጎ (1ዜና 22:14፤ 2ዜና 29:3-4) አስረከበው::

ይህ ለመሪዎች ትልቅ ነጥብ ነው:: መሪዎች መሥራት ያለባቸው እግዚአብሔር የወሰነላቸውን (የመጠነላቸውን) የሥራ ድርሻ፤ መጓዝ የሚጠበቅባቸውም እርሱ የለካላቸውን ርቀት መጠን ብቻ ነው:: አንድ ሰው እንዲሠራው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተፈቀደለትን መጠን ሳይተላለፍና የሌላውንም ድርሻ ለመንጠቅ ሳይሞክር በማገልገል የቀረውን ለቀጣዩ የሚያስረክብ መሆን አለበት::

ሰሎሞንም ቤቱን ከሠራ በኋላ የቀደመውን በማስታወስ ስለዚህ ሁኔታ ሲናገር «ዳዊት ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ስም ቤት ይሠራ ዘንድ በልቡ አሰበ:: እግዚአብሔርም ...ለስሜ ቤት ትሠራ ዘንድ በልብህ አስበሃልና ይህን በልብህ ማሰብህ መልካም አደረግህ:: ነገር ግን ከወገብህ የሚወጣው ልጅህ እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል እንጂ ቤት የምትሠራልኝ አንተ አይደለህም አለው» (1ነገ 8:17-19) ይላል:: ከዚህ እንደምናስተውለው ለዳዊት ጥያቄ የእግዚአብሔር መልስ ሁለት ክፍል ነበረው::

- 1ኛው - ቤት ልትሠራልኝ ያሰብኸው ሃሳቡ ጥሩ ነው::

- 2ኛው - ቤቱን የምትሠራልኝ ግን አንተ አይደለህም የሚል ነው::

የእግዚአብሔር አሠራር:- ትክክለኛን ነገር በትክክለኛ መንገድ (ወይም በትክክለኛ ሰው) መሥራት ነው:: የመንግሥቱን ሥራ ለሠራተኞች አከፋፍሎ የሚሰጥ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ አንድ መሪ እግዚአብሔር በዘላለማዊ ዕቅዱ ውስጥ:-

- በእኔ ዘመን ምን ሊሠራ ይወድዳል?
- ለእኔ የሚሰጠኝ የሥራ ድርሻ ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ አለበት::

እንግዲህ እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት እግዚአብሔር የሰጠውን የሥራ ድርሻ ብቻ የሠራ ሰው ነው:: በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ በእርሱ የተፈቀደልንን ድርሻ መፈጸም ይገባል:: አገልግሎት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ነውና::

## 7. ዳዊት:- እግዚአብሔርን የሚጠይቅና በእርሱ የሚታመን መሪ::

የእግዚአብሔርን ሀሳብ በዘመኑ ያገለገለው ዳዊት (ሐዋ 13:36) አንዱ የሚታወቅበት ባሕርዩ ሊያደርግ ለሚያስበው ነገር አስቀድሞ የአምላኩን ፈቃድ መጠየቁ ነው:: «ዳዊትም:- ልሂድን? እነዚህንስ ፍልስጥኤማውያን ልምታን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ» (1ሳሙ 23:2):: ከዚህ ጊዜ በፊት ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን በጦርነት ገጥሞ ነበር:: ያውም ጎልያድን ገጥሞ ድልም አድርጓል (1ሳሙ 17:50):: ስለዚህ ፍልስጥኤማውያንን በሰልፍ መግጠም ለዳዊት የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም:: ሆኖም በራሱ የቀደመ ልምድ አልታመነም:: ሁልጊዜ ምሪትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጠይቃል::





ዳዊት ከነገሠ በኋላም «ልውጣን? በእጄስ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ» (2ሳሙ 5:19):: እግዚአብሔርም ዳዊትን «ውጣ» (5:19) አለው:: ደግሞም በሌላ ሁኔታ «በኋላቸው ዞረህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት ግጠማቸው» (5:23) በማለት የውጊያ ስትራቴጂ ሰጠው:: እንዲሁም «የሽውሽውታ ድምፅ ስትሰማ በዚያን ጊዜ ቸኩል» (5:24) በማለት ጊዜውን አመለከተው:: ያ ሰዓት እግዚአብሔር ለዚህ ሥራ የሚነሣበት ሰዓት ነው ማለት ነው::

በጦርነት ድል ለማግኘት የጠላትን አሰላለፍ ማወቅና ጊዜን መምረጥ አስፈላጊ ነው:: ተፋላሚው በሚደክምበት በኩል በተገቢው ሰዓት መግባት ለድል ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል:: ይህን ሁሉ የሚያውቅ እግዚአብሔር በየትኛው አቅጣጫና መቼ መሄድ እንዳለበት ለዳዊት ነገረው:: ድል የሚገኘው እግዚአብሔር በሚነሣበት ጊዜ በመነሣት፤ እርሱ በሚዋጋበት በኩል አብሮ በመሰለፍ ነው::

በሌላም ጊዜ «ዳዊት:- ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ ልውጣን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ:: እግዚአብሔር ውጣ አለው:: ዳዊትም:- ወዴት ልውጣ? አለ:: እርሱም:- ወደ ኬብሮን ውጣ አለው (2ሳሙ 2:1):: የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል የሚፈልግ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይጠይቃል፤ ያንኑም ያደርጋል::

በወጣትነቱና በስደት ዘመኑ አምላኩን መጠየቅ የለመደው ዳዊት ይህ መልካም ባሕርይው አድጎበት በንጉሥነት ዘመኑም (ትልቅ ሰው ከሆነም በኋላ) እግዚአብሔርን ይጠይቅ ነበር:: በእስራኤል ላይ ቀጥሎ ቀጥሎ ራብ በሆነ ጊዜ ራቡ የሆነው ለምንድን ነው? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ:: ያ ራብ ለምን እንደሆነ እግዚአብሔር መልስ ሰጠው (2ሳሙ 21:1-2):: ከ300 ዓመት ያህል በፊት ኢያሱ ለገባዖን ሰዎች የገባውን ቃል ኪዳን ሳአል ስላፈረሰ የመጣ ራብ

ነበር፡፡ ሳኦልም ከሞተ 30 ዓመት ያህል ሆኖታል፡፡ እግዚአብሔርን የጠየቀ ዳዊት የችግሩን ምንጭ ተረዳ፡፡

በአጠቃላይ፡- የዳዊት አንዱ የመሪነት ባሕርዩ ምሪት (ምክር) መጠየቁ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ምሪት ይጠይቃል (ለምሳሌ 2ሳሙ 5፡17-19) እንዲሁም ከሰዎች ምክር ይጠይቃል (ዜና 13፡1-4)፡፡ ዛሬም ቢሆን ሰልፉ የእግዚአብሔር እንደሆነ የሚያውቅ አገልጋይ የጌታውን ሀሳብ ያገለግላልና በየቀኑ የእርሱን ፈቃድ ይጠይቃል፡፡ እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ልናውቅ ከምንፈልገው በላይ እርሱ ፈቃዱን ሊያሳውቀን ፈቃደኛ ነው፡፡

ዳዊት እግዚአብሔርን መጠየቅ ብቻ ሳይሆን በተገለጠለት ጊዜ ያንን ለማድረግ የሚተጋ መሪ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ መጠየቅ አይበቃም፤ ለተገለጠው ፈቃድ መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የተገለጠ ሀሳቡን እንዲሁም ወደ እርሱ በጸሎት በመቅረብ መንፈስ ቅዱስ የሚገልጠውን ያንን በታማኝነት መፈጸም ይገባል፡፡ እግዚአብሔርን ከጠየቅነው ለገለጠው ነገር ልንታዘዝ ይገባልና፡፡

በአጠቃላይ በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያገለገለው ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማወቅና ለማድረግ ትጋት ነበረው፡፡ ንጉሥ ዳዊት ታላቁን እግዚአብሔርን በሕይወቱ ላይ ያነገሠ፤ የሕይወቱ ራስ፤ መሪ፤ መንገድ የሚያሳይ፤ የሚደግፍ እንደሆነ የተገነዘበ ሰው ነው፡፡ እንዲሁም በመሪነት የመጀመሪያውና ዋናው ቁም ነገር የሕዝቡ መሪ እግዚአብሔር መሆኑን በማወቅ ከእርሱ ምሪት በመጠየቅ መምራት ነው፡፡





## 8. ዳዊት፡- በእግዚአብሔር ደስ የሚለውና በሙሉ ኃይሉ የሚያመልክ ንጉሥ፡፡

ንጉሡ ሳኦል አርባውን የንጉሥነት ዘመኑን የጨረሰው ስለ እግዚአብሔር ታቦት ሳያስብ ነበር፡፡ በሳኦል ዘመን ታቦቱ በነበረበት ነው የቀረው፤ ያስታወሰው አልነበረም፡፡ ሳኦል እድሜውን የገፋው እግዚአብሔር የቀባውን ሲያሳድድ ነበር፡፡

ዳዊት በሰደትና በመንከራተት ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር አስቦት ወደ ዙፋን ሲመጣ ያደረገው የመጀመሪያ ነገር የእግዚአብሔር ታቦት ከተጣለበት አንስቶ ወደ ኢየሩሳሌም ማምጣት ነበር፡፡ ዳዊት ወደ መንግሥት ሲመጣ ይህ የመጀመሪያ አጀንዳው ነበር፡፡ ከዚያም ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለመሥራት ፈለገ፡፡

የእስራኤል ሞገሷ እግዚአብሔር በመካከሏ መገኘቱ መሆኑን የተረዳው ዳዊት በብሉይ ኪዳን የመገኘቱ ምሳሌ (ምልክት) የሆነውን ታቦቱን ወደ ዋና ከተማው ለማምጣት ተነሣ፡፡ ታቦቱን በሰው እንደሚመጣ አንድ ዕቃ አድርጎ አልቆጠረውም፡፡ ለካህናት ብቻም አልተወውም፡፡ ራሱ ሄዶ ሊያመጣው ወደደ፡፡ በሚመጣበትም ጊዜ በታላቅ ደስታ ራሱ በእግዚአብሔር ፊት ይዘምር፤ ይዘል፤ በሙሉ ኃይሉ ይጫወት ነበር፡፡

እግዚአብሔርን የሚያከብር ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጥ ሰው ነው፡፡ «የሳኦል ልጅ ሜልኮል ...ንጉሡም ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘፍን አየች፤ በልብዋም ናቀችው» (2ሳሙ 6፡16)፡፡ ዳዊት ግን ያከበረውን፤ ሥልጣን የሰጠውን አምላኩን እግዚአብሔርን የሚያከብር ምንም ነፍስ የማይቀርለት ሰው ነበር፡፡ ለሜልኮል «...አለቃ እሆን ዘንድ ...የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ» (6፡21) በማለት መለሰላት፡፤ ለእርሷም አልበጀችትም፤

«ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም» (6:23)::

እንዲሁም ዳዊት በጋድ በኩል መሠዊያ እንዲሠራ እግዚአብሔር ሲያዝዘው (2ሳሙ 24:18) «ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም» (2ሳሙ 24:24) በማለት ዋጋ ከፍሎ ታዘዘ:: እግዚአብሔርን ማምለክ፤ ማክበርና መታዘዝ ያውቃል::
መሪዎች በምንም ደረጃ ላይ ቢሆኑ በኃያሉ እግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ ሊያደርጉ ያስፈልጋል:: መሪዎች የአምልኮና የዝማሬውን ተግባር «ለሌሎች» ዘማሪዎች ወይም አገልጋዮች ሳይተዉ ራሳቸው በእግዚአብሔር መገኘት ፊት የሚዘምሩ፤ የሚንበረከኩ፤ ክብርን የሚሰጡ ሰዎች መሆን አለባቸው:: በአገልግሎት ለቀዳሚው ተግባር ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል፤ ይህም አምልኮ ነው:: ይህ ደግሞ የመሪ ቀዳሚ ተግባሩ ነው:: ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት የሚዘምር «እግዚአብሔር ኃይሌ ዝማሬዬ ነው» (መዝ 118:14) የሚል በእግዚአብሔር ደስ የሚለው ሰው ነው:: እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርሱ መዘመር ደስታው ነው::

## 9. ዳዊት:- እስራኤልን አንድ ያደረገ፤ የቤተ መቅደስ አምልኮን ያደራጀ መሪ::

እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ኪዳን ሲያደርግ «ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ» (ዘፍ 15:18) ያለው የተፈጸመው ዳዊት እስራኤልን አንድ አድርጎ ባስተዳደረበት ዘመን ነበር:: ዳዊት «በእስራኤል ሁሉና በይሁዳ ላይ ...ነገሠ» (2ሳሙ 5:5):: እንዲሁም «በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የነበረውን ግዛት» (8:3) በመያዝ «በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ» (2ሳሙ 8:15) ተብሏል::





ዳዊት ተስፋውን ለመጨበጥ የተዋጋና የተስፋውን ሙላት ያየ ሰው ነው:: ኢያሱና ከእርሱ በኋላ የተነሡት መሳፍንት ሳአልንም ጨምሮ ያልያዙትን የተስፋ ምድር ዳዊት ተዋግቶ አገኘው::

«የእስራኤል አምላክ እንዳዘዘ፤ አባታቸው አሮን እንደ ሰጣቸው ሥርዓት ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገቡበት የአገልግሎታቸው ሥርዓት ይህ ነበር» (1ዜና 24:19) እንደሚል በአሮን ዘመን የጀመረ የአገልግሎት ሥርዓት ነበር:: ዳዊት ደግሞ በአሮን ዘመን የተጀመረውን የአምልኮ ሥርዓት በማጠናከር አገልጋዮች በተራ እንዲሠሩ የሰሞንን አሠራር ሥርዓት ያስጀመረ ሰው ነው:: ይህም አገልጋዮች ሥራቸውን በተራ (በመፈራረቅ) እንዲሠሩ የሚያደርግ የአገልግሎት አደረጃጀት ነበር::

ዳዊት ለቤተ መቅደስ አገልጋዮች የሰጠውን የአገልግሎት ሥርዓትና ተራ ልጁ ሰሎሞን ጠብቆታል:: «የእግዚአብሔርም ሰው ዳዊት እንዲህ አዝዞ ነበርና፤ ካህናቱን እንደ አባቱ እንደ ዳዊት ሥርዓት በየአገልግሎታቸው ሰሞን[17] ከፈላቸው፤ ሌዋውያንም እንደ ሥርዓታቸው ...የሰሞናቸው ከፈላቸው፤ በረኞቹንም ...በየሰሞናቸው ከፈላቸው» (2ዜና 8:14) ይላል::

ስለ መዘምራን አደረጃጀት ጥቂት ደግሞ እንመልከት:: «አራቱ ሺህም ለምስጋና በተሠሩት በዜማ ዕቃዎች እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር» (1ዜና 23:5):: ከእነዚህ በዜማ ዕቃ ከሚያገለግሉ አራት ሺህ መዘምራን በፊትና በሁለተኛ ተራ የሚቆሙ (1ዜና 15:17-19)፤ «በመሰንቆ ምሥጢር ነገር ያዜሙ» (15:20) የነበሩ፤ በጽናጽል የሚያገለግሉ (15:19)፤ «ስምንት አውታር ባለው በገና» (15:21) ይዘምሩ የነበሩ ነበሩ:: መዘምራን አለቃና ዜማ አስተማሪም

[17] ሰሞን እንደ ቃሉ አገባብ ክፍል ወይም ተራ ማለት ነው::

ነበራቸው:: «የሌዋውያኑም አለቃ ከናንያ በዜማ ላይ ተሾሞ ነበር:: ብልሃተኛ ነበርና ዜማ ያስተምራቸው ነበር» (15:22) እንደሚል::

እግዚአብሔር ሥርዓት ይሰጣል፤ ሥርዓቱን ለማወቅና ለመጠበቅ እንደ ዳዊት አስተዋይ መሪ ያስፈልጋል:: ይህ «የሰሞን» የአሠራር ሥርዓት ከዳዊት በኋላ ከአንድ ሺህ ዓመታት በላይ ዘልቆ ካህኑ ዘካርያስ «በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፤ እንደ ካህናት ሥርዓት ...» (ሉቃ 1:8-9) እንደሚል በአዲስ ኪዳን መጀመሪያም ላይ ታይቶአል::

ለአሠራር ሥርዓት ማበጀትና ማደራጀት ትልቅ ጥበብ ነው:: ከመሪዎች ኃላፊነት አንዱ መልክ ያለው አሠራር እንዲኖር በማድረግ ውጤታማ ተግባርና አገልግሎት እንዲከናወን ማድረግ ነው::

## 10. ዳዊት:- በእግዚአብሔር ትምህርት ቤት ተምሮ ያለፈ ጥሩ ተማሪ::

ዳዊት በነቢዩ ሳሙኤል እጅ ንጉሥ እንዲሆን ከተቀባ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ዙፋን አልመጣም:: በዳዊት ሕይወት የደረሱት ትልልቅ መከራዎች የሆኑት ከተቀባ በኋላ ወደ ዙፋን እስከሚመጣበት ባለው ጊዜ ነበር:: ያለፈባቸውን ሁኔታዎች በጥቂቱ እንደሚከተለው እንመልከት::

ዳዊት ጎልያድን ከገደለ በኋላ ሳኦል ዳዊትን «ተመቅኝቶ ተመለከተው» (1ሳሙ 18:9):: ዳዊትን ለመግደል «ጦሩን ወረወረ:: ዳዊትም ሁለት ጊዜ ከፊቱ ዘወር አለ» (19:11):: በውኑ ዳዊት ጦር ይወረወርበት ዘንድ ምን አደረገ? ሳኦልን (እስራኤልን) ከፍልስጥኤማውያን ስላዳነ (19:4-5) መሞት አለበትን?





ሳኦል በዳዊት ቀንቶአልና ለመግደል «ተጠበበ»:: ልጁን አጋባሃለሁ በሚል ሰበብ «ሳኦልም ዳዊትን በፍልስጥኤማውያን እጅ ይጥለው ዘንድ አሰበ:-...» (18:25) ወደ እነርሱ ላከው:: ሳኦል እንደተመኘው ዳዊት በፍልስጥኤማውያን እጅ ሳይወድቅ ተመለሰ:: «ሳኦልም እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር እንደሆነ አየ» (18:28):: ይህን ሁሉ እያወቀ ሳኦል ግን ዳዊትን ለመግደል ከማሴር አላቆመም::

በሌላም ጊዜ ሳኦል «ዳዊትን ጠብቀው በነጋው እንዲገድሉት መልከተኞቹን ወደ ዳዊት ቤት ላከ፤ ሚስቱም ሜልኮል:- በዚህች ሌሊት ነፍስህን ካላዳንህ ነገ ትገደላለህ ብላ ነገረችው:: ሜልኮልም ዳዊትን በመስኮት አወረደችው፤ ሄዶም ሸሽቶም አመለጠ» (19:11-12):: ሳኦል ልጁን ሜልኮልን የዳረለት እንድታጠምድለት ነበር (18:21):: እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ነበርና ለወጥመድነት የተዘጋጀችውን ሰው የምታስመልጥ (መሸሎኪያ በር) አደረገለት::

ዳዊት ሸሽቶ ወደ አርማቴም ወደ ሳሙኤል መጣ:: «የሳኦልም ቁጣ ነደደ እርሱም ደግሞ ወደ አርማቴም መጣ» (19:22):: በማሳደዱ በመቀጠል ዳዊትን ሊገድለው ፈለገ የእግዚአብሔር መንፈስ ለሳኦል ሌላ ሥራ ሰጠው (19:23-24)::

ከዚያ በኋላ በቤተ መንግሥት እንዲቀመጥ ተቀብቶ የነበረው ዳዊት «በምድረ በዳ በአምባ ውስጥ ይኖር ነበር» (23:14):: አሳዳጁ «ሳኦልም ሁልጊዜ ይፈልገው ነበር፤ እግዚአብሔር ግን በእጁ አሳልፎ አልሰጠውም» (23:14)::

ሳኦል ዳዊትን በምድረ በዳ በማሳደድ «ሳኦልም በተራራው በአንድ ወገን ሄደ፤ ዳዊትና ሰዎቹም በተራራው በሌላ ወገን ሄዱ:: ሳኦልና ሰዎቹም ዳዊትንና ሰዎቹን ለመያዝ ከብበዋቸው ነበርና ዳዊት ከሳኦል ፊት ያመልጥ ዘንድ ፈጠነ» (23:26):: ዳዊት በሳኦል ሊያዝ በተከበበበት ወቅት ድንገት «ወደ ሳኦልም መልእክተኛ መጥቶ:-

ፍልስጥኤማውያን አገሩን ወርረውታልና ፈጥነህ ና አለው:: ሳኦልም ዳዊትን ማሳደድ ትቶ ተመለሰ» (23:27):: ይህ ለሳኦል አጋጣሚ የሚመስል ነገር ለዳዊት ግን እግዚአብሔር ያዘጋጀው «ማስመለጥ» ነው:: «የዚያ ስፍራ ስም የማምለጥ ዓለት ተባለ» (23:28)::

ታዳጊው እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚታደግበት መንገድ ልዩ ልዩ ነው:: ጦር ሲወረወር ዞር በማድረግ (18:11)፤ እንደ ሜልኮል ለማጥመድ የተላከውን «አስመላጭ» በማድረግ፤ ለመማረክ ለተዘጋጀው «ሌላ ተልዕኮ» በመስጠት፤ እንደ እስራኤላውያንና ግብጻውያን እየተያዩ እንዳይገናኙ ዐምድን በማቆም (ዘጸ 14:20) ወዘተ. ይሆናል::
እግዚአብሔር ከመረጠውና አካሄዱን ከእርሱ ጋር ከሚያደርግ እንዲሁም የእርሱን ጊዜ ጠብቆ በፈቃዱ ለመኖር ከሚወስን ሰው ጋር አብሮ ይሆናል:: የእግዚአብሔር ትምህርት ቤት በቤተ መንግሥት፤ በምድረ በዳ፤ በስደት፤ በጦርነት ስፍራ ሁሉ ነው::

ዳዊት የተራበበትም ጊዜ ነበር (1ሳሙ 22)፤ አእምሮ እንደጎደለው የሆነበትም ጊዜ ነበረ (1ሳሙ 21:13):: በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ነበር (1ሳሙ 16:18፤ 18:12፤14፤ 2ሳሙ 5:10፤ 8:6፤ 1ዜና 17:8):: ወደ ንጉሥነት ሲያመጣው «...አንተ መንጋውን ስትከተል በሕዝቤ በእስራኤል ላይ አለቃ ትሆን ዘንድ ከበግ ጥበቃ ወሰድሁህ፤ በሄድክበትም ሁሉ ከአንተ ጋር ነበርኩ» (2ሳሙ 7:8-9) አለው::

በእግዚአብሔር ለአገልግሎት የተመረጠ (የተቀባ) ሰው ሰዓቱ እስኪሞላ ድረስ ሊሰደድ ይችላል:: እግዚአብሔር እስከጊዜው አሳዳጆችንም ዝም ይላቸዋል:: ለሚያስተውል ሰው ግን ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ነው:: ዳዊት ለንጉሥነት የሰለጠነው በዚህ መንገድ ነበር::






በማጠቃለል:- ዳዊት ከነገሥታት ሁሉ በኩር (መዝ 89:27) የሆነ የነገሥታት የበላይ ተደርጎ የሚቆጠር ሰው ነው:: ስለዚህም በምሳሌነት ስለ እርሱ ብዙ ተነግሯል:- የዳዊት መክፈቻ፤ የዳዊት ድንኳን፤ የዳዊት ዙፋን፤ የዳዊት ቅርንጫፍ፤ የዳዊት ከተማ፤ የዳዊት ኃያላን (2ሳሙ 13:13-17) በሚል ተገልጾአል:: ኢየሱስ ክርስቶስም የዳዊት ልጅ ነው:: ዳዊት በእስራኤል ዘንድ የታወቀ ታላቅ ንጉሥ ነው::

ዳዊት በእረኝነቱ፤ በዘማሪነቱ፤ በጀግንነቱ፤ በጦር መሪነቱ ይታወቃል:: ዳዊት በእስራኤል ዘንድ መልካም ባለ ቅኔ በመባል (2ሳሙ 23:1) ይታወቃል:: ዳዊት በገናን አሳምሮ ይጫወት ነበር (1ሳሙ 16:18-23):: በቤተ መቅደስም ውስጥ የአምልኮ ሥርዓትን አደራጀ (1ዜና 6:31)፤ ብዙ መዝሙሮችን ጻፈ (2ሳሙ 1:17-23):: የሙዚቃ መሣሪያዎችም በእርሱ ስም ይጠሩ ነበር (አሞ 6:5፤ ዕዝ 3:10፤ ነህ 7:24፤46):: በዚህ ሁሉ ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገለገለ::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዳዊት ከሚናገረው መካከል «ዳዊት በዘመኑ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አድርጎ ነበርና፤ ካዘዘውም ነገር ሁሉ ፈቀቅ አላለም ነበርና» (1ነገ 15:5) የሚለው በብሉይ ኪዳን በተደጋጋሚ የተገለጸ ቃል ነው:: አዲስ ኪዳን የዳዊትን ሕይወት የሚያጠቃልለው «ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ...» (ሐዋ 13:36) በማለት ነው::

ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸሎት ሲያስተምር «ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» (ማቴ 6:10) በሉ አለ:: የአገልግሎት ከፍተኛው ደረጃ እግዚአብሔር የሚፈልገው በምድር እንዲፈጸም ማገልገል ነው:: ዳዊት በዘመኑ ባለፈበት መንገድ በጦር ሜዳ፤ በንጉሥነት፤ በማደራጀት፤ ቤተ መቅደስ ሊሠራ አስቦ «አትሠራልኝም» ሲባል በመታዘዝ፤ ወዘተ.

የእግዚአብሔርንዘ ሀሳብ አገለገለ:: ክርስቲያናዊ መሪነት ይኸው ነው::



ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገለገለ (ሐዋ 13:36)

በ3ኛው ሺህ ኢትዮጵያ የምትገኝ አንተ እንደ ዳዊት ሁሉ ባለህበት ዘመንና ቦታ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ተረድተህ እንድታገለግል ተጠርተሃል::





ምዕራፍ 4

# ሕዝቅያስና ኢዮስያስ

## 4.1 ሕዝቅያስ

ሕዝቅያስ የይሁዳ ንጉሥ የነበረው የአካዝ ልጅ ነው (2ነገ 18:1-2፤ 2ዜና 29:11):: አካዝ «እንደ አባቱም እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አላደረገም» (2ዜና 28:1) የተባለለት ሰው ነበር:: «የይሁዳም ንጉሥ አካዝ እግዚአብሔርን ከዷልና፤ ከእርሱም እጅግ ርቆአልና እግዚአብሔር ስለ እርሱ ይሁዳን አዋረደው» (28:19)። አካዝ ይሁዳን ለአሥራ ስድስት ዓመት ሲገዛ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ የዘጋ፤ በምድሪቱ የጣዖት አምልኮን ያበረታታ፤ ታላቅ መንፈሳዊ ውድቀትን ያመጣ ንጉሥ ነበር::

ሕዝቅያስ በሀያ አምስት ዓመት ዕድሜው መንገሥ ሲጀምር በይሁዳ ታላቅ መንፈሳዊ ውድቀት ነበረ:: ቤተ መቅደሱ ለረጅም ዘመን ተዘግቶና ቆሽሾ ነበር:: ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን በመውደዱና በመፍራቱ በይሁዳ ምድር የነበረውን መንፈሳዊ ውድቀት መልክ ለመቀየር፤ ቤተ መቅደሱንም ለማጽዳትና መንፈሳዊ ተሐድሶን ለማምጣት ተነሣ:: አባቱ የቤተ መቅደስ በሮች እንዲዘጉ አድርጎ ነበርና የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ የቤተ መቅደሱን በሮች

መከፈት ነበር:: ይህ የሕዝቅያስ የመጀመሪያ እርምጃ መሆኑ የአመራሩን ትኩረትና አቅጣጫ አመልካች ነው:: ይሁዳን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ እንዳሰበ ያመለክታል::

ከዚያ በኋላ ሕዝቅያስ ለካህናትና ሌዋውያን የጥሪያቸውን ታላቅነት ያስገነዝባቸዋል:: ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲቀድሱና እርሱን እንዲያገለግሉት፤ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ያደፋፍራቸዋል (2ዜና 29:3-36):: እነዚህ ካህናትና ሌዋውያን ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲመሩና ሕጉን እንዲያስተምሩ አስቀድሞ ራሳቸውን ማንጻት፤ ራሳቸውንም ለእግዚአብሔር መለየት ይገባቸዋል:: ከዚያም ካህናቱና ሌዋውያኑ ቤተ መቅደሱን አጸዱ::

በአባቱ ዘመን የፈረሰውን ለማደስና የተረሳውን አምልኮ ለማስጀመር ሕዝቅያስ ይህንን ሁሉ ከየት አየው? ከማንስ ተማረው? ብሎ ያስጠይቃል:: ብዙ ጊዜ ልጆች ከአባቶቻቸው ባዩት ይቀጥላሉና:: አባቱ ክፉ ንጉሥ ስለ ነበረ ሕዝቅያስ ከአባቱ የተማረው መልካም ነገር አይኖርም:: ሆኖም ገና በወጣትነቱ ልቡን ወደ እግዚአብሔር መለሰ፤ ፈለገውም:: ቤተ መቅደሱን ከፈተ፤ በምድሪቱ የነበረውንም ጣዖት አጠፋ::

እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን የሚጠብቅ አምላክ እንደሆነ የሚያውቅ መሪ አስቀድሞ ከእርሱ ጋር ያለውን የግል ኅብረት በንስሐ ያድሳል፤ ከእርሱም ጋር ይስማማል:: ሕዝቅያስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ ቃል ኪዳንን ያደሰ ሰው ነበር:: እንዲሁም ሌሎች አገልጋዮች ወደየአገልግሎታቸው እንዲመለሱና እንዲሰማሩ ያደፋፈረና ብዙዎችን ለሥራው ያነሳሣ መሪ ነበር::

የሕዝቅያስ ተሐድሶ በምድሪቱ ላይ የተደረገው በስፋትና በጥልቀት ነበረ:: ሕዝቅያስ ምድሪቱን የሚያረክሱ የአምልኮ ቦታዎችን ሁሉ ያጸዳ፤ የማምለኪያ አጸዶችን የቆረጠ ሰው ነው (2ነገ 18:3-7፤ 2ዜና






29):: በሙሴ ዘመን እስራኤላውያን በምድረ በዳ በእባብ በተነደፉ ጊዜ ሰዎች እይተውት ይድኑ ዘንድ እግዚአብሔር በሰጠው ትእዛዝ መሠረት የተሠራው የናስ እባብ (ዘኍ 21:9) በሕዝቅያስ ዘመን በሕዝቡ ይመለክ ስለነበር ሕዝቅያስ ይህንንም ሰበረ፤ አቃጠለ (2ነገ 18:4፤ 2ዜና 31:1)::

## ሕዝቅያስ መንፈሳዊ ተሐድሶና ምድሪቱን ማጽዳት

(2ዜና 29-31)




ሕዝቅያስ የጀመረውን ተሐድሶ ያጠናቀቀው የፋሲካን በዓል በማድረግ ነበር (2ዜና 30):: ተረስቶ የነበረውን የፋሲካ በዓል

እንደገና ለማክበር ሲዘጋጅ በይሁዳ የሚኖሩትን የእስራኤል ነገዶች ሁሉ እንዲገኙ ጠራቸው፡፡

የተሐድሶው ሂደት የሚከተሉትን ዋና ክፍሎች ያጠቃልላል (2ዜና 29-30፤ 2ነገ 18)፡፡

1. የእግዚአብሔርን ቤት ደጆች ከፈተ፤ አደሳቸውም።
2. ካህናቱንና ሌዋውያኑ ለአገልግሎት እንዲቀደሱ አነሳሳ
3. የእግዚአብሔርን ቤት ማንጻትና መቀደስ ተከናወነ
4. ለእስራኤል ሁሉ ማስተስረያ የኃጢያቱን መሥዋዕት ቀረበ
5. መዘምራኑ የእግዚአብሔር መዝሙር ዘመሩ አጐነበሱም ሰገዱም።
6. ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጡ ወደ እስራኤልና ወደ ይሁዳ ሁሉ ላከ- «አንገተ ደንዳና አትሁኑ፤ እጃችሁንም ለእግዚአብሔር ስጡ» አላቸው
7. የንስሐ ጊዜ ሆነ፤ «እያሌ ሰዎች ሰውነታቸውን አዋረዱ፥ ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ»።
8. ቃል ኪዳኑን አደሱ፡፡ የቂጣውን በዓል በታላቅ ደስታ በኢየሩሳሌም አደረጉ፤
9. የኮረብታው መስገጃዎችና መሠዊያዎች አፈረሱ፡፡ «የእስራኤልም ልጆች ...ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ፤ ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው» (2ነገ 18፡4)፡፡
10. የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ተዘጋጀ።

ሕዝቅያስ በነገሠ በአሥራ አራተኛው ዓመት የአሦር ንጉሥ ሰናክሬም ይሁዳን ለመውሰድ መጣ፡፡ «በውኑ ያለ እግዚአብሔር ትእዛዝ ይህን ስፍራ አጠፋ ዘንድ ወጥቻለሁን? እግዚአብሔር ወደዚች አገር ወጥተህ አጥፋት አለኝ» (2ነገ 18፡25) በማለት የእግዚአብሔር መልእክተኛ አድርጎ ራሱን አቀረበ፡፡ እንዲሁም ሕዝቅያስ «እግዚአብሔር ያድነናል ብሎ ቢያታልላችሁ አትስሙት»





(2ነገ 18፡32) በማለትም አሦራውያን መልእክተኞቹ በአይሁድ ላይ «በታላቅ ድምፅ በዕብራይስጥ ቋንቋ ይጮኹባቸው ነበር» (2ነገ 18፡26፤ 2ዜና 32፡17-18)፡፡ በተጨማሪም የሕዝቅያስ አምላክ ሕዝቡን ከእጄ ያድን ዘንድ አይችልም የሚል ደብዳቤ ጻፈ። በዚህ ወቅት ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ ሕዝቡንም አጽናናቸው፡፡

ሕዝቅያስ በነገሠበት ሀያ ዘጠኝ ዓመት ውስጥ በይሁዳ መንፈሳዊ ተሐድሶን ከማምጣት አንስቶ ሌሎች ታላላቅ ሀገርን (ሕዝብን) የሚጠቅሙ የልማት ሥራዎች አከናውኗል፡፡ ግብርናውና ንግዱ እንዲስፋፋ፤ ለምርቱም በተመረጡ ቦታዎች ማከማቻ እንዲኖር አድርጎአል (2ዜና 32፡27-28)፡፡ ኢየሩሳሌም በቂ ውሃ እንድታገኝ (32፡30) እንዲሁም የሀገር ጥበቃም እንዲጠናከር (32፡5-7) ያደረገ ንጉሥ ነበር፡፡

ከሕዝቅያስ ሕይወት ስለ መሪነት የሚከተሉትን እናስተውላለን፡፡

## 1. ሕዝቅያስ፡- መንፈሳዊ ተሐድሶ ለማምጣት የቆረጠ መሪ፡፡

ሕዝቅያስ ከእርሱ በፊት ከነበሩት መሪዎች የተማረው መልካም ምሳሌ ባይኖርም እንኳ ገና ወደ ንጉሥነት እንደመጣ መንፈሳዊ ተሐድሶ ለማምጣት የቆረጠ ሰው ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት ለውጥ ለማምጣት የሚያስከፍለው ከፍተኛ ዋጋ ቢኖርም ሕዝቅያስ ግን አባቱ ይሄድበት ከነበረው በተለየ መንገድ በመሄድ ምድሪቱን ከጣዖት አምልኮ ለማጽዳት ቆርጦ ተነሣ፡፡ ተሐድሶውን በምድሪቱ የጀመረው በነገሠ በመጀመሪያው ወር በመሆኑ ይህ ወደ ንጉሥነት እንደመጣ የመጀመሪያው አጀንዳ መሆኑን ያሳያል፡፡ መንፈሳዊ መሪነት ከሁሉ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት የሚያጠናክር በሕዝቡ መካከል መንፈሳዊ ጤናማነትን የሚጠብቅ ነው፡፡

## 2. ሕዝቅያስ፡- መንፈሳዊ ተሐድሶው እንዲቀጥል ያደራጀ መሪ፡፡

ሕዝቅያስ የተቋረጠውን የቤተ መቅደስ አምልኮ በማስጀመርና የፋሲካ በዓል በማድረግ ቃል ኪዳን ካደሰ በኋላ የተጀመረው መልካም ነገር የሚቀጥልበትን ሥርዓት አበጀ፡፡ አስቀድሞ የተበታተኑና አገልግሎታቸውን የረሱ አገልጋዮችን ያሰባሰበውና ያነሳሳው «አሁንም የቍጣው ጽናት ከእኛ እንዲመለስ ከእስራኤል አምላክ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አደርግ ዘንድ በልቤ አስቤአለሁ። ልጆቼ ሆይ፥ በፊቱ ትቆሙና ታገለግሉት ዘንድ፥ አገልጋዮቹም ትሆኑ ዘንድ፥ ታጥኑለትም ዘንድ እግዚአብሔር መርጦአችኋልና ቸል አትበሉ» (2ዜና 29፡10-11) በማለት ነበር፡፡

አገልጋዮቹ በብዙ ጥረት ከተሰባሰቡና ራሳቸውን ለአገልግሎት ከቀደሱ በኋላ ደግሞ በጥሩ አደረጃጀት እንዲቀጥሉ ‹የካህናትንና የሌዋውያንን ሰሞን በየክፍላቸውና በየአገልግሎታቸው አቆመ› (2ዜና 31፡2)፡፡ እንዲሁም «በእግዚአብሔርም ቤት ለአገልግሎት እንዲጸኑ ለካህናቱና ለሌዋውያን ክፍላቸውን ይሰጡ ዘንድ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ሕዝብ አዘዘ» (31፡4)። ከዚያም አሥራትና በኩራት እንዲቀርብና በሥርዓት እንዲያዝ አለቆችን ሾመ፡፡ ለአገልጋዮችም የሚገባቸውን ይሰጡ ነበር፡፡ የሕዝቡ ሕይወት በመታደሱና ቃል ኪዳኑን ከአምላኩ ጋር በማደሱ ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገባውም ‹ከምር› ሆነ፡፡ ስለዚህም ዋነኛው ካህን «ሕዝቡ ቍርባኑን ወደ እግዚአብሔር ቤት ማቅረብ ከጀመረ ወዲህ በልተናል፥ ጠግበናልም፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ባርኮአልና ብዙ ተርፎአል፤ የተረፈውም ይህ ከምር ትልቅ ነው ብሎ ተናገረ» (31፡10)።

ተሐድሶ ለቅጽበታዊ ጊዜ ቦግ ብሎ የሚጠፋ እሳት እንዳይሆን የሚቀጥልበትን ሥርዓት ማበጀትና ማደራጀት ለእሳቱ የማያቋርጥ ማገዶ እንደማቅረብ ነው፡፡ በአንድ ወቅት የታየ መልካም ጅማሬና





መነቃቃት እንዲቀጥል መሪዎች ስለ አገልጋዮች አገልግሎት ብቻ ሳይሆን ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ስለማሟላት በሩቁ ማሰብና በእቅድ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ መንፈሳዊ ተሐድሶና መነቃቃት ለአገልጋዮች መንፈሳዊ በረከትን እንደሚያመጣ ሁሉ ለኑሮ የሚያስፈልገውንም ያትረፈርፋል፡፡

## 3. እንደ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን የሚወድ መሪ ሲኖር የመንፈስ አንድነት ያድጋል፡፡

የሕዝቅያስ ዘመን እስራኤል ይሁዳና እስራኤል በሚል በሁለት ተከፍላ የነበረችበት ዘመን ነው፡፡ እርሱ የይሁዳ ንጉሥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በይሁዳ ምድር መንፈሳዊ መነቃቃት ሲጀምር ሕዝቅያስ ይኸው ለእስራኤልም እንዲደርስ አደረገ፡፡ ምንም እንኳ ይሁዳና ቀሪው የእስራኤል ክፍል በአስተዳደር የተለያዩ ቢሆንም ለረጅም ዘመን ተረስቶ የነበረው የፋሲካ በዓል በይሁዳ ሲደረግ ሌሎች የእስራኤል ነገዶች ሁሉ በበዓሉ ላይ እንዲገኙ ጥሪ አደረገላቸውና ተገኙ (2ዜና 30፡1-7)፡፡ የእውነተኛ መንፈሳዊ ተሐድሶ አንዱ መለያው የቅዱሳንን ኅብረት በማጠናከሩ ነው፡፡ ፍቅር «ድንበር ይዘላል»፡፡

## 4. እንደ ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን የሚፈራ መሪ መኖር ከቤተ ክርስቲያን አልፎ ለምድርም በረከት ይሆናል፡፡

ሕዝቅያስ የተሐድሶውን ሥራ ቤተ መቅደሱን ከማጽዳትና አምልኮውን ከማደስ አልፎ ወደ ምድር ሁሉ እንዲደርስ ያደረገ ሰው ነበር፡፡ በመሠረቱ የመንፈሳዊ መሪዎች አገልግሎት (ወይም መልካም ተጽዕኖ) በቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን አይኖርበትም፡፡ በቤተ ክርስቲያን የሚደረገው መልካም ነገር ሁሉ ወደ ምድር ያልፋል፡፡ ሕያው ቃሉ «በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፤ ፊቴንም ቢፈልጉ፤ ከክፉ

መንገዳቸውም ቢመለሱ፤ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፤ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፤ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ» (2ዜና 7፡14) እንደሚል የእግዚአብሔር ሕዝብ ለምድር መፈወስ ምክንያት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነተኛ መንፈሳዊ ተሐድሶ ሲኖር ለምድርም የሚተርፍ በረከት ያመጣል። ስለዚህ የመንፈሳዊ መሪ መልካም ተጽዕኖው በሚመራው ድርጅት ወይም ቤተ ክርስቲያን ላይ የተገደበ ሳይሆን አልፎ የሚሄድና ወደ ምድር የሚደርስ ነው።

## 5. ሕዝቅያስ በችግር ጊዜ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ታምነው እንዲጸኑ የመከረ መሪ።

ሰናክሬብ ይሁዳን ለመውረር ባሰበና ደብዳቤም ለሕዝቅያስ በላከ ጊዜ ሕዝቅያስ «...ወደ እግዚአብሔር ቤት ወጥቶ በእግዚአብሔር ፊት ዘረጋው። ...እንግዲህም አምላካችን አቤቱ፥ የምድር መንግሥታት ሁሉ አንተ ብቻ እግዚአብሔር አምላክ እንደ ሆንህ ያውቁ ዘንድ ከእጁ እንድታድነን እለምንሃለሁ» (2ነገ 19፡14-19፤ ኢሳ 37፡20) ብሎ ጸለየ። የእግዚአብሔር አምላክነት እንዲታወቅ መሻት ሙሴ (32፡12፤ ዘዳ 9፡26-29) እንዲሁም ዳዊት (መዝ 59፡13፤ 83፡18) ከጸለዩት ጋር ይመሳሰላል።

ሕዝቅያስ ሕዝቡንም «ጽኑ፤ አይዞአችሁ፤ ከእኛም ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው ይበልጣልና ከአሦር ንጉሥና ከእርሱ ጋር ካለው ጭፍራ ሁሉ አትፍሩ፤ አትደንግጡም። ከእርሱ ጋር የሥጋ ክንድ ነው፤ ከእኛ ጋር ያለው ግን የሚረዳንና የሚዋጋልን አምላካችን እግዚአብሔር ነው ብሎ አጽናናቸው። ሕዝቡም በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ቃል ተጽናና» (2ዜና 32፡7-8)።

እንዲሁም ወደ ነቢዩ ኢሳይያስም መልእክተኞች ላከ። እግዚአብሔርም በኢሳይያስ በኩል «...ስለ ሰደቡኝ፤ ስለ ሰማኸው





ቃል አትፍራ። እነሆ፤ በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ፤ ወሬንም ይሰማል፤ ወደ ምድሩም ይመለሳል፤ በምድሩም በሰይፍ እንዲወድቅ አደርገዋለሁ በሉት አላቸው» (2ነገ 19፡6-7)። በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ከአሦራውያንም ሰፈር ብዙዎችን ገደለ። እንዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ታደገ። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን አደረገ (ኢሳ 37፡32)።

መንፈሳዊ ሥራ ሁልጊዜ መከናወንና ድል አይሆንም። በአመራሩ ላይ ከውጭና ከውስጥ የሚነሳ ተቃውሞ ወይም ጠላት የሚያስነሳው ፈተና ሊመጣ ይችላል። የክርስቲያንዊ መሪ ጥንካሬው ራሱ በእግዚአብሔር ታምኖ የሕዝቡ ልብ በአምላኪ እንዲጸና የሚያበረታታ ሲሆን ነው።

## 6. ሕዝቅያስ፦ አጨራረሱ ደካማ የሆነ መሪ።

ሕዝቅያስ እስከ ሞት ድረስ በታመመ ጊዜ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል «ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል» (2ነገ 20፡1) አለው። ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እጅግ አድርጎ አለቀሰ። እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማ እንባውንም አየ ፈወሰውም፤ በዕድሜውም ላይ አሥራ አምስት ዓመት ጨመረለት። ለመፈወሱም ምልክት እንዲሆን «ፀሐይም በጥላ ስፍረ ሰዓት ላይ የወረደበት አሥር ደረጃ ወደ ኋላ ተመለሰ» (ኢሳ 38፡8፤ 2ነገ 20፡11) ተብሏል። በኢያሱ ዘመን ፀሐይና ጨረቃ እንዲቆሙ ሆኗል አሁን ደግሞ ጊዜን ወደ ኋላ በመወስድ እግዚአብሔር ድንቅ አሳየ። ከዚህ ፈውስና ተአምራት በኋላ «ሕዝቅያስ ግን እንደ ተቀበለው ቸርነት መጠን አላደረገም፤ ልቡም ኰራ፤ ስለዚህም በእርሱና በይሁዳ በኢየሩሳሌምም ላይ ቍጣ ሆነ» (2ዜና 32፡25) ተብሎአል።

ሕዝቅያስ ግን ከእግዚአብሔር የተጨመረለትን «ተጨማሪ ዕድሜ» በአግባቡ አልተጠቀመበትም:: የውስጥ ጓዳውን የእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር ከባቢሎን ለመጡ ጎብኚዎች አሳያቸው (2ነገ 20:12):: በዚህም እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል ቁጣውን ሲገልጽ:- «በዘመኔ ሰላምና እውነት ይሁን አለ» (ኢሳ 39:8፤ 2ነገ 20:19)። ሕዝቅያስ «በራሴ ዘመን» ማለቱ ከራሱ ዘመን በኋላ ለይሁዳ ስለሚሆነው ግዴለሽ እንደነበረ ያመለክታል:: ስለ ዕድሜው መጨመርና ስለ ግል ደኅንነቱ ብቻ ያሰበ ሰው ነው:: በወጣትነት አጀማመሩ «ድንቅ» የተባለ መሪ በሽምግልናው አጨራረሱ ለረጅም ዘመን የሚሆን ለትውልድ የሚተላለፍ ሰላም እንዲኖር ባለማሰቡ «ደካማ» ሆነ:: መልካም እረኝነት ግን ቀጥሎ ስለሚመጣው ትውልድ ደኅንነት የሚያስብና ግድ የሚለው ነው::





# 4.2 ኢዮስያስ

በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት መልካም እንዳደረጉ ከተመሰከረላቸው ነገሥታት መካከል አንዱ ኢዮስያስ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢዮስያስ «እንደ ሙሴም ሕግ ሁሉ በፍጹም ልቡ በፍጹምም ነፍሱ በፍጹምም ኃይሉ ወደ እግዚአብሔርም የተመለሰ እንደ እርሱ ያለ ንጉሥ ከእርሱ አስቀድሞ አልነበረም፤ እንደ እርሱም ያለ ንጉሥ ከእርሱ በኋላ አልተነሣም» (2ነገ 23:25) ይላል:: እንዲሁም በ2ዜና 34:2 «በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ፤ በአባቱም በዳዊት መንገድ ሄደ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አላለም» ተብሎአል::

በይሁዳ ብዙ ነገሥታት ቢነግሡም በዳዊት መንገድ እንደሄዱ የተነገረላቸው ግን በቁጥር ጥቂት ናቸው:: አንዳንዶቹ አጀማመራቸው ጥሩ ሆኖ አጨራረሳቸው ያላማረ ነበር:: አንዳንዶቹ ደግሞ ተግባራቸው መልካም ሆኖ በፍጹም ልብ እንዳላደረጉት የተነገረላቸው ናቸው (ለምሳሌ አሜስያስ 2ዜና 25:2):: «በፍጹም ልቡ በፍጹምም ነፍሱ በፍጹምም ኃይሉ ወደ እግዚአብሔርም የተመለሰ» የተባለለት ኢዮስያስ ምን ዓይነት ሰው ቢሆን ነው?

የሕዝቅያስ ልጅ ምናሴ መንገሥ በጀመረ ጊዜ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረ:: በኢየሩሳሌም አምሳ አምስት ዓመት ነገሠ። ይህ ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ ረጅሙ ዘመን ነው:: ምናሴ ከነገሥታት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ። «ለሰማይም ሠራዊት ሁሉ ሰገደ፤ አመለካቸውም» (2ዜና 33:3)። ምናሴ እስራኤልን አሳተ። ሆኖም «በተጨነቀም ጊዜ አምላኩን እግዚአብሔርን ፈለገ፤ በአባቶቹም አምላክ ፊት ሰውነቱን እጅግ አዋረደ፤ ወደ እርሱም ጸለየ፤ እርሱም ተለመነው፤ ጸሎቱንም ሰማው፤ ወደ መንግሥቱም ወደ ኢየሩሳሌም መለሰው፤ ምናሴም እግዚአብሔር እርሱ አምላክ

እንደ ሆነ አወቀ» (33፡12-13) ተብሎለታል። ከምናሴ በኋላ ልጁ አሞጽ ነገሠ:: አሞንም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሠራ (2ነገ 21፡20)::

ኢዮስያስ የአሞን ልጅ የምናሴ የልጅ ልጅ ነው (2ነገ 21፡23-30):: የኢዮስያስ አያትና አባት እግዚአብሔርን የማይፈሩ ጣዖትን የሚያመልኩ ንጉሦች ነበሩ:: እንደ ሕዝቅያስ ሁሉ ኢዮስያስ ከአባቱ መልካም ነገርን አልተማረም:: ኢዮስያስ በነገሠበት ጊዜ በምድሪቱ ላይ የበዓል አምልኮ ተንሰራፍቶ ነበር (2ዜና 34፡3፤ ኤር 25፡3፤11፤29):: ኢዮስያስ ሥር የሰደደና ብዙ ተከታዮችን ያፈራ የባዕድ አምልኮን ለመለወጥ የተነሳ ሰው ነበር::

ኢዮስያስ የይሁዳ ንጉሥ የሆነው ገና በስምንት ዓመቱ ነበር:: በይሁዳ ለሰላሳ አንድ ዓመት ነገሠ:: በአሥራ ስድስት ዓመቱ እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ:: የኢዮስያስ የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔርን መፈለግ ነበር:: እግዚአብሔርን በመፈለግ የጀመረው ኢዮስያስ ከነገሠ ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ በሀገሪቱ ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶን ማምጣት ጀመረ:: ሀገሪቱን ከጣዖት አምልኮ ለማጽዳት ተነሣ:: ከወላጆቹ ንጉሥነትን ብቻ እንጂ ባዕድ አምልኮን አልወረሰም::

ኢዮስያስ በሃያ ስድስት ዓመቱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንዲታደስ ትእዛዝን አወጣ:: ሥራውም በጥሩ ዝግጅት ተጀመረ:: የማደሱ ሥራ እንደ ተጀመረ ለረጅም ዘመን የተረሳ (የተተወ) የሕግ መጽሐፍ አገኙ:: መጽሐፉ ሲነበብ ይሁዳ የገባችበትን የመንፈሳዊ ዝቅጠት መጠን ለማየት ተቻለ:: ኢዮስያስ ይሁዳን ከወደቀችበት መንፈሳዊ አዘቅት ለማውጣትና የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ለማደስ ሕዝቡን ሁሉ አነሳሣ:: የተጀመረው ተሐድሶ በፍጥነትና በጥልቀት እንዲደረግ የሕጉ መጽሐፍ መገኘት ምክንያት ሆነ::





የኢዮስያስን የተሐድሶ እርምጃ በሦስት ደረጃዎች ማየት እንችላለን::

የመጀመሪያው:- ራሱ እግዚአብሔርን መፈለግ መጀመሩ ነበር:: ከነገሠ ከስምንት ዓመት በኋላ በአስራ ስድስት ዓመቱ እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ (2ዜና 34፡3)::


ሁለተኛው:- ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ምድር ከጣዖታት ማንጻት መጀመሩ ነበር:: ኢዮስያስ በሀያ ዓመት ዕድሜው ኢየሩሳሌምንና ይሁዳን ከጣዖታት ያጸዳው የማምለኪያ አጸዶችን በመቁረጥና ጣዖቶችን ሁሉ በመሰባበር ነበር (2ዜና 34፡3-7):: የኢዮስያስ የተሐድሶ እርምጃ በስፋት ምድሪቱን የሸፈነ ነበር:: ተሐድሶው ከይሁዳ ወደ ተለዩት ወደ ሰማርያ አልፎ ሄደ:: ተሐድሶው እርሱ ላለበት አካባቢ ብቻ ሳይሆን በሩቅ ላሉት ሁሉ መድረስ አለበት ብሎ የተነሣና እግዚአብሔርም ያከናወነለት ሰው ነው::

ሦስተኛው:- በሀያ ስድስት ዓመቱ ቤተ መቅደሱ መታደስ ተጀመረ:: የመታደሱ ሥራ በታላቁ ካህን ኬልቅያስ መሪነት ተጀመረ:: ቤተ መቅደሱን በማጽዳቱና በማደሱ ሥራ ላይ እያሉ የሕጉ መጽሐፍ ተገኘ (2ዜና 34፡14-15):: አያቱ ምናሴ እግዚአብሔርን እጅግ አስቆጥቶት ነበርና በእስራኤል ላይ መከራ ነበር:: ስለዚህም ኢዮስያስ «አባቶቻችን በእርስዋ የተጻፈውን ሁሉ ይሠሩ ዘንድ የዚህችን መጽሐፍ ቃል ስላልሰሙ በላያችን የነደደ የእግዚአብሔር ቍጣ እጅግ ነውና ሄዳችሁ ስለ እኔና ስለ ሕዝቡ ስለ ይሁዳም ሁሉ የዚህችን የተገኘችውን መጽሐፍ ቃል እግዚአብሔርን ጠይቁ ብሎ» (2ነገ 22፡13) ወደ ነቢይቱ ሕልዳና ላከ:: እግዚአብሔር «በፊቴም ራስህን አዋርደሃልና፤ በዚህም ስፍራና በሚኖሩበት ላይ ቃሌን በሰማህ ጊዜ ራስህን አዋርደሃልና፤ ልብስህንም ቀድደህ በፊቴ አልቅሰሃልና እኔ ደግሞ ሰምቼአለሁ»

(2ዜና 34:27):: እንዲሁም «በዚህም ስፍራ ላይ የማመጣውን ክፉ ነገር ዓይኖችህ አያዩም» (2ነገ 22:20) አለው።

የኢዮስያስን የተሐድሶ እንቅስቃሴና ቅደም ተከተል በሚከተሉት ሥዕላዊ መግለጫዎች እንመለከታለን::

ኢዮስያስ ቤተ መቅደሱን ያጸዳበትና ምድሪቱን ያደሰበት አካሄድ (2ዜና 34)




ከኢዮስያስ ሕይወትና አመራር የምናስተውላቸው ቁልፍ ነገሮች አሉ::

1. ኢዮስያስ:- እግዚአብሔርን ፈለገ ቃል ኪዳንንም አደሰ::
ኢዮስያስ ገና በልጅነቱ (ወጣትነቱ) እግዚአብሔርን መፈለግ ጀመረ (2ዜና 34:3):: ቀዳሚ እርምጃው ራሱ «እግዚአብሔርን ተከትሎ ይሄድ ዘንድ፤ ትእዛዙንና ምስክሩንም ሥርዓቱንም በፍጹም ልቡና በፍጹም ነፍሱ ይጠብቅ ዘንድ፤ በዚሁም መጽሐፍ የተጻፈውን የቃል ኪዳን ቃል ያጸና ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን





አደረገ» (2ነገ 23:3፤ 2ዜና 34:31):: ከዚህም በኋላ ሕዝቡ ሁሉ ቃል ኪዳን ገቡ::


ኢዮስያስ ለጥሩ አጀማመር መልካም ምሳሌ ነው:- ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔርን መፈለግ ከእርሱም ጋር መጣበቅ:: እግዚአብሔርን መፈለግና እርሱን መውደድ ለመንፈሳዊ ባሕርይ የመጀመሪያው ደረጃ ነው:: መንፈሳዊ መሪነት የሚጀምረው የግል ሕይወትን በማስተካከልና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ ነው::

ከአባት (ወይም ከቀደሙት መሪዎች) የተወረሰን ክፉ ነገር አፍርሶ መልካም የሆነ አዲስን ነገር ለመጀመር ታላቅ ድፍረትና የመሪነት ጥበብ ይጠይቃል:: ይህ የሚጀምረው አስቀድሞ በግል እግዚአብሔርን በመፈለግ ነው::

2. የተሐድሶ ግብ ንፁህ አምልኮን መመለስ ነው::
ኢዮስያስ ታላቅና ሰፊ የሆነውን የተሐድሶ ሥራ የጀመረው ጣዖት አምልኮንና ርኩሰትን ሁሉ ከምድሪቱ በማስወገድና በማንጻት ነበር (23:5፤ 2ዜና 34:3፤5፤6፤8፤33):: ቤተ መቅደስን፤ መሠዊያውንና ምድሪቱን ከጣዖት፤ ከርኩሰት ማንጻት የተሐድሶ ክፍል ነው:: እግዚአብሔርና ጣዖት በአንድ ላይ አይኖሩም:: ከተቀደሰው ስፍራ ርኩሰት መወገድ አለበት::

ቤተ መቅደሱንና ምድሪቱን የማንጻት ሥራ ደረጃ በደረጃ ተደርጎ ምድሪቱን ሸፈነ:: ከዚያ በኋላ የቀደመው አምልኮ ተመለሰ:: ተሐድሶ ሲጀመር አድማሱ ሩቅ ግቡም ትልቅ መሆን አለበት:: የተሐድሶ ግብ የእግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘት፤ የእርሱ መከበርና የንጹሕ አምልኮ መጀመርና መቀጠል ነው::

ብዙ ሕዝብ የሚከተለውን በመሻርና በተቃራኒው በመሄድ መንፈሳዊ ተሐድሶን ለማምጣትና ለውጥን ለማካሄድ መሞከር ከማዕበሉ አቅጣጫ በተቃራኒው እንደ መቅዘፍ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ‹ትራንስፎርሜሽናል› የመሪነት ሥራ በእግዚአብሔር ላይ መታመንን ይጠይቃል::




## 3. ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀ አንድ ሰው ታላቅ ለውጥ ያመጣል::

ኢዮስያስ የወረሰውና በዕድሜው ዘመን የተመለከተው ክፉ ሆኖ ሳለ መልካምን ነገር በማድረግ ከእግዚአብሔር ወገን ለመቆም በድፍረት





ተነሳ:: በአባቶቹ የነበረው ጣዖት አምልኮ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍ ሰንሰለቱን የበጠሰና ንጹሕ አምልኮን ወደ ይሁዳ የመለሰ ንጉሥ ነበር::

እግዚአብሔርን የሚፈራና ከእርሱ ጋር ተስማምቶ የሚሠራ የራሱም የግል አጀንዳ የሌለው መሪ ሲነሣ ለምድር የሚበቃ መንፈሳዊ ተሐድሶና በረከት ሊያመጣ እንደሚችል ከኢዮስያስ ሕይወት መገንዘብ ይቻላል:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሚስማማ አንድ ሰው ጋር ስለሚሆን ይከናወንለታል:: ፈቃዱን ለአምላኩ በማስገዛቱ ምክንያትም በእጁ እንዳለ መሣሪያ ስለሚሆንለት ምድርን የሚሞላ ሥራ ይሠራበታል::

## 4. የእውነተኛ ተሐድሶ መለኪያው የእግዚአብሔር ቃል ነው::

ኢዮስያስ ተሐድሶን የጀመረው የሕጉ መጽሐፍ ባልተገኘበት ጊዜ ነበር:: የሕጉ መጽሐፍ በተገኘ ጊዜ ይሁዳ የወደቀችበትን ደረጃ አሳያቸው:: የሕጉን መጽሐፍ ማንበባቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አመለከታቸው:: ስለዚህም ኢዮስያስ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመጠየቅ ወደ ነቢይቱ ሕልዳና ላከ:: እግዚአብሔርም መልስ ሰጠው:: የሕጉን መጽሐፍ እንደ መለኪያ (ቱንቢ) በማድረግ ተሐድሶውን እንደ ተጻፈው አደረጉ:: የተሐድሶ ትክክለኛነት ሚዛኑና መለኪያው የእግዚአብሔር ቃል ነው::

## 5. እውነተኛ ተሐድሶ አድማሱን ያሰፋል::

ብርሃን በጨለማ ላይ እንደሚያበራ እውነተኛ ተሐድሶም እንዲሁ ነው:: በይሁዳ በኢዮስያስ የተጀመረው ተሐድሶ በዚያን ዘመን እርሱ በሚያስተዳድረው ቦታ ብቻ ሳይሆን አልፎ ወደ ቤቴልና ሰማርያ ዘለቀ:: ለውጡ ወደ ብዙ ቦታ ተዳረሰ::

## 6. የውጭ መታደስ ከውስጥ መታደስ ይጀምራል።

የኢዮስያስ ሀገርን የሚሸፍን መንፈሳዊ ተሐድሶና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የጀመረው በራሱ ሕይወት ነው። አስቀድሞ የታደሰው ራሱ ኢዮስያስ ነው። ዘላቂነት ያለው መንፈሳዊ ተሐድሶ የሚኖረው መሪው ራሱ የታደሰ ሆኖ ሲገኝና በእውነተኛ መንፈሳዊነት በምሳሌነት ሲመራ ነው። ይህ በባሕር ላይ እንደሚወድቅ ጠብታ (ወይም ጠጠር) ነው። ጠብታው ሲያርፍ ካረፈበት ቦታ ጀምሮ ወደ ውጭ ክቦችን[18] እየሠራ እንደሚሄድ ከውስጡ በእርግጥ የታደሰ ሰው ሲኖር ዙሪያውን በለውጥ ያንቀሳቅሳል።

## ኢዮስያስ እግዚአብሔርን ባለመስማቱ በቀስት ተገደለ።

የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ኒካዑ ከአሦር ንጉሥ ጋር ሊጋጠም ሲሄድ በመንገድ ኢዮስያስ በጦርነት ገጠመው። ኒካዑ ኢዮስያስን «...እግዚአብሔርም እንድቸኩል አዝዞኛል፤ ከእኔ ጋር ያለው እግዚአብሔር እንዳያጠፋህ ይህን በእርሱ ላይ ከማድረግ ተመለስ ብሎ መልእክተኞችን ላከበት። ኢዮስያስ ግን ይዋጋው ዘንድ ተጽናና እንጂ ፊቱን ከእርሱ አልመለሰም፤ በእግዚአብሔርም አፍ የተነገረውን የኒካውን ቃል አልሰማም» (2ዜና 35፡21-22)። ቀስተኞችም ንጉሡን ኢዮስያስን ወጉት፤ ሞተም።

ኢዮስያስ በፍጹም ልቡ እግዚአብሔር መከተል የጀመረ ሰው ነበር። በእጁም ታላቅ ተሐድሶ ተደርጓል። በስተመጨረሻው ግን የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማት በቀስት ተወግቶ ሞተ። በመንፈሳዊ መሪነት ስለ ጅማሬ ብቻ ሳይሆን ስለ አጨራረስ መጠንቀቅ እንደሚገባ ይህ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። ታላላቅ የሚባሉ መሪዎች በወንበር ላይ ለረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ እንደ ቀድሞው

[18] Ripples/ Concentric circles





ዘመን በትሕትና መሄድና እግዚአብሔርን በፍጹም ልባቸው መታዘዝ እየተዉ መጨረሻቸው ያላማረ ጥቂት አይደሉም።

በማጠቃለል፡- ሕዝቅያስ ለኢዮስያስ የአያቱ አባት ነው። ወይም ኢዮስያስ የሕዝቅያስ የልጅ ልጅ ልጅ ነው። በሁለቱ መካከል የ60 ዓመት ያህል ልዩነት አለ። ሕዝቅያስና ኢዮስያስ ተመሳሳይ ባሕርይ አላቸው። ሁለቱም ወደ እግዚአብሔር ተመልሰዋል፤ ሁለቱም ታላቅ ሀገራዊ መንፈሳዊ ተሐድሶን መርተዋል፤ ሁለቱም ከአባቶቻቸው የወረሱት መልካም መንፈሳዊ ነገር አልነበረም።

በሁለቱም የታየው የመጀመሪያ እርምጃ እግዚአብሔርን መፈለግ ነበር። መንፈሳዊ ተሐድሶ የሚጀምረው ከአዳሹ ከእግዚአብሔር ጋር በመስማማትና እርሱን በመፈለግ ነው። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የተከማቸውን ቆሻሻ በማጽዳት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቃል ኪዳን ማደስ የመልካም እረኛ ተቀዳሚ ተግባር ነው። እንዲሁም ሀገር በእግዚአብሔር ትባረክ ዘንድ ምድርን ከርኩሰት ማጽዳት ይገባል። መንፈሳዊ ተሃድሶ ማድረግ ምድር ከጥፋት ተጠብቃ በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ እንድትሆን መንፈሳዊ አጥር ማበጀት ነው።

## ምዕራፍ 5

# ነህምያ

አይሁድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቃል ኪዳን ባለመጠበቃቸው በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጥቷቸው ነበር፡፡ በ605 ዓ.ዓ. የባቢሎን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ወረረ (2ነገ 24፡1)፡፡ በ586 ዓ.ዓ. ከተማዋን ከነቤተ መቅደሱ አፈረሰ (2ዜና 36፡17-19)፡፡ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ እንደተናገረው ከ70 የምርኮ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምድራቸው መለሰ (ኤር 29፡10-14)፡፡

የምርኮው ዘመን ሲፈጸም የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ አይሁድ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ፈቀደ (2ዜና 36-22-23፤ ዕዝ 1-14)፡፡ እግዚአብሔርም የሕዝቡን መንፈስ አስነሣ (ዕዝ 1፡5)፡፡

እግዚአብሔር የዘላለም ሀሳቡን ለመፈጸም በራሱ አሠራርና ጊዜ በየዘመናቱ መሪዎችን ሲያስነሣ ኖሯል፡፡ ነህምያ ያከናወነው ቅጥር ማደስ ሥራ ሌሎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች በተለያየ ጊዜ የየድርሻቸውን ያከናወኑት ታላቅ ሥራ ክፍል ነበር፡፡

በዘሩባቤል መሪነት 50000 ያህል ሕዝብ በ537 ዓ.ዓ. ተመለሰ፡፡ የተመለሱት መሠዊያውን አደሱ፤ ቤተ መቅደሱን ለመሥራትም መሠረት ጣሉ፡፡ የሚያግዙአቸውም የእግዚአብሔር ነቢያት ነቢዩ ሐጌና ነቢዩ ዘካርያስ ነበሩ (ዕዝ 6፡14-15)፡፡ በተነሣው ተቃውሞ





ሥራው ለአሥር ዓመት ያህል ከተስተጓጎለ በኋላ የቤተ መቅደሱ ሥራ በ516 ዓ.ዓ. ተጠናቀቀ፡፡

ነቢዩ ሐጌ «በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን? አሁንም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ። ...ወደ ተራራው ውጡ፤ እንጨትንም አምጡ፤ ቤቱንም ሥሩ፤ እኔም በእርሱ ደስ ይለኛል፤ እኔም እመሰገናለሁ፤ ይላል እግዚአብሔር» (ሐጌ 1፡3-8) የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ለዘሩባቤል ያመጣ ሰው ነው፡፡ ነቢዩ ዘካርያስም «...በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፤ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ታላቅ ተራራ ሆይ፤ አንተ ምንድር ነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ» (ዘካ 4፡6-7) የሚለውን መልእክት ለዘሩባቤል አመጣ፡፡

የምርኮኞች ሁለተኛው መመለስ የሆነው ቤተ መቅደሱ ከተጠናቀቀ ከ58 ዓመታት ያህል በኋላ ነበር፡፡ በካህኑ ዕዝራ መሪነት 2000 ያህል ወንዶችና ቤተሰቦቻቸው በ458 ዓ.ዓ. ተመለሱ፡፡ የሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት ታደሰ፤ አምልኮም በቤተ መቅደስ ተጀመረ፡፡

ሦስተኛው ተመላሽ በነህምያ መሪነት የመጣው ኢየሩሳሌም በባቢሎን ከተማረከች ከ160 ዓመት፤ ዘሩባቤል ከተመለስ ከ90 ዓመትና ዐዝራ ከተመለስ ደግሞ ከ13 ዓመት ያህል በኋላ በ444 ዓ.ዓ. ነበር፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመሪነታቸው ጥበባቸውና ጽናታቸው ከታወቁ ሰዎች መካከል አንዱ ነህምያ ነው፡፡ ነህምያ በእግዚአብሔር በመታመን ታላቅን ሥራ ለመጀመር የደፈረ፤ ለረጅም ዓመታት ፈርሶ የቆየን ቅጥር ያደሰ፤ ሕዝቡን ወደ ቀድሞ መንፈሳዊ ሕይወት የመራ፤ የጸሎትና የተግባር ሰው ነው፡፡

ነህምያ በምርኮ በነበረበት ምድር በንጉሥ ፊት የሚያስቆም ከፍተኛ ሥልጣንና የታማኝነት ስፍራ ነበረው፡፡ ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ በሰማ ጊዜ የተመቻቸ ኑሮውን ትቶ የፈረሰውን ለማደስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ አሰበ፡፡ ከንጉሡ ፈቃድ በመጠየቅም የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፡፡

ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ሁኔታ፤ ስለ ቅጥሩ መፍረስና ስለ በሮቹ በእሳት መቃጠል ከወንድሙ ከአናኒ ከሰማ በኋላ (ነህ 1፡1-4) የመጀመሪያ እርምጃው ይህንን ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ፣ መጸለይ ነበር (1፡5-11)፡፡ በጸሎቱም ስለ ራሱና ስለ አባቶቹ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ ገባ፡፡ ለእስራኤላውያን መበተንና ለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ምክንያቱ ኃጢአት መሆኑን ነህምያ ተረድቷል፡፡ ስለዚህ በጸሎቱ የደረሰው ሁሉ የሆነው እግዚአብሔርን ካለመስማትና ኪዳንን ካለመጠበቅ የተነሣ እንደሆነ ይገልጻል፡፡

ነህምያ በጸሎቱ የገለጸው ለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ «መንፈሳዊ ምክንያት» መኖሩን ነው፡፡ ይህ በገሃዱ ዓለም ከሚቀርበው ትንታኔና የታሪክ ጸሐፊዎች ከሚዘግቡት ምክንያት የተለየ ነው፡፡ በጸሎቱ የተናገረው በየዘመናቱ ስለተነሡ ነገሥታትና ኃያላን፤ ስለ ተሰለፈው ሠራዊት ብዛትና አሰላለፍ እንዲሁም ማሸነፍና መሸነፍ አልነበረም፡፡

ነህምያ ከንጉሡ ፈቃድ አግኝቶ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄደ በኋላ የመጀመሪያው ተግባሩ የፈረሰውን ራሱ መመልከት ነበር (2፡11-16)፡፡ ራሱ ብቻውን የፈረሰውን ተዘዋውሮ ካየ በኋላ በኢየሩሳሌም ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር በልቡ ያኖረውን ለሕዝቡ ነገራቸው (2፡17-18)፡፡ ሕዝቡንም ለሥራው በማነሳሳት ከእርሱ ጋር አብረው የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሠሩ አደፋፈራቸው፡፡





ለረጅም ዘመን ፈርሶ የቆየው የኢየሩሳሌም ቅጥር ፈርሶ እንዲኖር እንጂ እንዳይታደስ የሚፈልጉ የእግዚአብሔር ቤት ጠላቶች የነህምያን መምጣት ሲሰሙ ተበሳጩ፤ በታላቅ ተቃውሞ ተነሱበት፡፡ ቅጥሩን ሊሠሩ ባሰቡትም ላይ ጦቢያ፤ ሰንበላጥና ጌሳም በንቀት ሳቁባቸው (2፡19)፡፡

ነህምያ ቅጥሩን የማደስ ሥራ የጀመረው በመጀመሪያ ሥራን ለሠራተኞች በማከፋፈል ነበር፡፡ እያንዳንዱ የሥራ ድርሻ እንዲኖረውና ማን የትኛውን እንደሚያድስ መደበ፡፡ ሁሉም በእድሳቱ ሥራ ላይ ተሰማሩ፡፡ የቅጥሩ መታደስ እንደ ተጀመረ የነጦቢያ ተቃውሞ እየበረታና መልኩን እየለዋወጠ መጣ (4፡1-5)፤ ሠራተኞችን ለማሸበር (ለመግደልም) አሰቡ (4፡7-9)፡፡ እዚህ ላይ የነህምያ ትልቅ የመሪነት ኃላፊነት ሕዝቡ ሀሳቡ እንዳይበታተን፤ የእድሳቱም ሥራ እንዳይስተጓጎል ትኩረቱን በሥራው ላይ እንዲያደርግ ማድረግ ነበር፡፡ ነህምያም ሠራተኞች በሥራው ላይ እጃቸውን እንዲያበረቱ መከራቸው፤ እግዚአብሔርም መከናወንን ሰጣቸው (4፡16-23)፡፡

የነህምያ መሪነት የታየው በቅጥሩ ሥራ ላይ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን ማኅበራዊ ግንኙነት ፍትሐዊ በማድረግም ነበር፡፡ በማደሱ ተግባር ከሕዝቡ ጋር አብሮ ስለሚውል ሕዝቡ ያለበትን የኑሮ ችግር ተገነዘበ፡፡ ሕዝቡ ከተበደረው (ዕዳ) ክብደት የተነሣ ተጎድቶ ነበርና ቅጥሩን ለማደስ አቅም አንሶት ነበር፡፡ ድሆችም ያጉረመርሙና ይጮኹ ነበር (5፡1-5)፡፡ ስለዚህ ነህምያ የሕዝቡን ችግር በቅርበት በመረዳት ዕዳቸው እንዲሰረዝ አስደረገ (6-13)፤ ራሱም ለአለቅነቱ የሚገባውን እንኳን ከሕዝቡ ባለመቀበል ለድሃ ያለውን ርኅራኄ በምሳሌነት አሳየ (14-19)፡፡

ለ120 ዓመት በላይ ፈርሶ የቆየው ቅጥር ከታደሰ በኋላ ነህምያ ቀጥሎ የወሰደው የመሪነት እርምጃ የሕዝቡ ሕይወት እንዲታደስ

ማድረግ ነበር:: ይህም የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ተጀመረ (7:73-8:12):: ሕዝቡም ወደ እግዚአብሔር በለቅሶ ተመለሰ (8:9):: ቃል ኪዳን ያፈረሰ ሕዝብ የቀደመውን ቃል ኪዳን አደሰ (9:38):: ይህ ታላቅ መንፈሳዊ ተሐድሶ ነው::

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ታላላቅ የተሐድሶ ሥራዎች ተከናውነዋል:: ቅጥሩ ታደሰ፤ በብድርና በዕዳ ምክንያት በብዙ ችግርና ጭኹት ይኖር የነበረው ሕዝብ ፍትሕ አገኘ፤ ሕዝቡም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳኑን አደሰ:: በመጨረሻም ታላቅ በዓል አደረጉ፤ ቅጥሩም ለእግዚአብሔር ተቀደሰ (12:27-43)::

ነህምያ መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣበት ጊዜ አንስቶ የቅጥሩ መታደስና የቃል ኪዳን ማደስ እስከተከናወነበት ድረስ ጊዜው አሥራ ሁለት ዓመት ነበር:: ከዚህ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ወደ ንጉሡ ተመለሰ (13:1-5):: ሆኖም በዚህ ጊዜ ውስጥ ሕዝቡ እንደገና በኃጢአት ውስጥ ገባ (13):: በዚህ ወቅት ቅጥሩ እንዳይታደስ የተቃወመው ጦቢያ በቤተ መቅደሱ ታላቁ ጓዳ ውስጥ መኖር ጀምሮ ነበር፤ ሕዝቡም በጋብቻ ከሌላ ሕዝብ ጋር ተደባልቆ ነበር:: ነህምያ ከሄደበት ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ (13:6-9) ቤተ መቅደሱንና ሕዝቡን ከእርኩስ ነገር የማጽዳት ሥራ ጀመረ::

የነህምያ የመሪነት ችሎታ የታየው በብዙ ዘርፍ ነበር:: በሕንፃ ሥራ፤ በማኅበራዊ ፍትሕ፤ ቃል ኪዳን በማደስና ሕዝብን ከተደባለቀ ነገር በማጥራት:: ነህምያ በመሪነት ችሎታው ኢየሩሳሌም ከጠላት እንድትጠበቅና የቀደመ ክብሯ እንዲመለስ፤ ሕዝቡ በሰላም እንዲኖርና የእግዚአብሔር ስም እንዲከበር ያደረገ ሰው ነው:: ስለዚህ የነህምያ የመሪነት ትኩረት መቀደስ፤ ንጽሕናና ፍትሕ ነው ማለት ይቻላል::






ከነህምያ አመራር የሚከተሉትን ጥቂት ነጥቦች አጉልቶ ማየት ይቻላል::

**1. መሪ ወደ ሥራ ከመሰማራቱ አስቀድሞ የችግሩን ትክክለኛ ምንጭ የሚረዳ ነው::**

ነህምያ የፈረሰው የኢየሩሳሌም ቅጥር ለማደስ ከመነሳቱ በፊት የችግሩን ምክንያት በትክክል የተገነዘበ ሰው ነው:: የኢየሩሳሌም ቅጥር የፈረሰው በጊዜው ኃያል በነበረችው ባቢሎን በ585 ዓ.ዓ. እንደነበረ በገሃዱ ዓለም የታወቀ ነው:: በመንፈሳዊው ዓለም ግን የኢየሩሳሌም ቅጥር እንዲፈርስ ምክንያት የሆነው የእስራኤል ልጆች ኃጢአት ነው (1:6)፤ እግዚአብሔር «ብትተላለፉ በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ» (1:8) እንዳለው አደረገ:: እንዲሁም የእግዚአብሔርን ነቢያት ስላልሰሙ፤ ስላቃለሉና ስላፌዙባቸው ስለዚህ ሰይፍ መጣባቸው፤ ለምርኮም አልፈው ተሰጡ (2ዜና 36:14-20):: ስለሆነም ለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ምክንያት በገሃዱ ዓለም የባቢሎን ኃያልነት ነው፤ በመንፈሳዊ ዓለም ግን የእስራኤላውያን ኃጢአት ነው:: በሚታየው ዓለም የሚከናወነው ድርጊት በመንፈሳዊው ዓለም የተከናወነውን ተከትሎ ነው::



ነህምያ እግዚአብሔርን የሚያውቅ መንፈሳዊ መሪ ስለሆነ ቅጥሩ የፈረሰው የእግዚአብሔር ጥበቃ ከሕዝቡ በመነሣቱ እንደሆነ ተረድቷል:: ቃል ኪዳኑን ለሚጠብቅ ሕዝብ እግዚአብሔር አጥሩ ነውና:: እግዘአብሔር ጥበቃውን ከሕዝቡ ላይ ሲያነሳ ሕዝቡ ለጠላትና ለመበተን የተጋለጠ ይሆናል (መዝ 80:12-13)::

ለችግሩ ትክክለኛውን ምክንያት የተገነዘበ መሪ ትክክለኛ እርምጃ ይወስዳል:: ነህምያ ለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ መንፈሳዊ ምክንያት እንዳለው የሚያውቅ ሰው ነው:: ስለሆነም የፈረሰን ቅጥር ለማደስ ከንጉሡ ፈቃድ ከመጠየቅ፤ ወደ ኢየሩሳሌም ከመሄድና ሥራ ከመጀመር በፊት ንስሐ ይቀድማል:: መንፈሳዊ መሪ ለችግሮች መንፈሳዊ ምክንያታቸውን ይፈልጋል:: ነህምያም ያደረገው ይህንኑ ነው:: መንፈሳዊ አመራር በዓለም ከሚገኘው አመራር የሚለይበት አንዱ መንገድ በዚህ ነው::

2. መንፈሳዊ መሪ ከእግዚአብሔር ራእይ የሚቀበልና የእቅድ ሰው ነው::

ነህምያ የመሪነት አገልግሎቱን የጀመረው በጸሎት ነው:: ነህምያ የፈረሰንና በእሳት የተቃጠለን ቅጥር የማደሻ መንገዱ በጾምና ጸሎት በኩል እንደሆነ ያወቀ፤ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለመረዳት መንገዱም በጸሎት እንደሚጀምር የተገነዘበ ታላቅ መሪ ነው::

ራእይ እግዚአብሔር ወደ ፊት በቅርብና በሩቅ ሊሆን የሚፈልገውን ነገር መረዳት፤ እርሱ ያየውን ማየት ነው:: ራእይ እግዚአብሔር ወደፊት እንዲሠራ ለሰው የሚሰጠው የሥራ (ወይም የተግባር) መገለጥ ነው:: ስለ ሥራው መገለጥን (ራዕይን/ መረዳትን/ ሸክምን) የሚሰጥ ራሱ እግዚአብሔር ነው:: ራእይ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መመሪያ፤ አጠቃላይ የሥራ ትእዛዝ (ወይም ንድፍ) በመሆኑ የሚገኘው እርሱን በመለመንና በመስማት ነው:: ራእይ የጸሎት ልጅ ነው፤ በጸሎት ይወለዳል፤ በጸሎት ያድጋል፤ በጸሎት ይከናወናል::

ጥሩ አመራር ግልጽ ከሆነ ሸክምና ራእይ ይጀምራል:: ነህምያ «እግዚአብሔርም ለኢየሩሳሌም አደርገው ዘንድ በልቤ ያኖረውን...» (2:12) እንዳለ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ምን መሥራት እንደሚገባው





እግዚአብሔር በልቡ አስቀምጦ ነበር:: ከዚህም ጋር ስለ ሥራው የተረዳው ነገር ነበር:: ይህም:-

- ሥራው ስንት ጊዜ እንደሚፈጅ (2:6)
- ካለበት ሥፍራ ወደ ኢየሩሳሌም እንዴት እንደሚኬድ (2:7)
- ሥራውን ለመሥራት ምን ዓይነት ዕቃ እንደሚያስፈልግ (2:8)

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ይህን ራእይ በልቡ ተሸክሞ ነው:: ይህንም ሸክም ከቦታው ጋር አገናዝቦ እየጸለየ በሥራ ላይ አዋለው::

ራእይ የተሰጠው ሰው ለተቀበለው ሸክም ባለ አደራ እንጂ ባለቤት አይደለም:: የራእዩ ባለቤት ሰጭው እግዚአብሔር ነው:: ተቀባዩ እግዚአብሔር በገለጠለት መጠን ለማከናወን የሚተጋ አገልጋይ ነው:: እግዚአብሔር የሥራው ባለቤት በመሆኑ ሠራተኛው የተቀበለውን ራእይ በሥራ ላይ የሚያውልበትን ጥበብ ከእርሱ መጠየቅ ይገባዋል:: ራእይ ተቀባዩንም ታላቅ መሪ የሚያሰኘው ራእይ መቀበሉ ሳይሆን የተቀበለውን ራእይ በጥንቃቄ መፈጸሙ ላይ ነው::

3. መሪ የሕዝቡን መንፈስ የሚያነሣሣና የሚያደራጅ ነው::

ነህምያ ኢየሩሳሌም እንደ መጣ አዋጅ አላስነገረም:: ነገር ግን በጸጥታ የፈረሰውን ዞሮ ተመለከተ (2:11-16)፤ የችግሩን መጠን ከወንድሙ ከሰማውና በልቡም ከተቀመጠው ሀሳብ ጋር በማገናዘብ አስቀድሞ የራሱን መረዳትና ግምገማ ወሰደ:: ጥሩ የሥራ እቅድ የሚዘጋጀው ከሌሎች በተገኘው መረጃ ላይ በመመሥረት ብቻ ሳይሆን እቅዱን የሚያዘጋጀው ሰው ራሱ በቦታው ተገኝቶ ቦታውን በማየት ስለ ሁኔታው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ሲኖረው ነው::

ነህምያ በልቡ የተቀመጠውን ሸክም ይዞ የፈረሰውን ቅጥር ከጎበኘ በኋላ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲጀምር መጀመሪያ ያደረገው በልቡ ያለውን ሸክም ለሕዝቡ መግለጽ ነበር (2፡13-17)። ሕዝቡ ያለበትን የውድቀት መጠን ተገንዝቦ ወደ እግዚአብሔር ልቡን እንዲያነሣ ካደረገ በኋላ በኅብረት «ተነሥተን እንሥራለን» (2፡20) አለ።

ታላቅ መሪ በልቡ ያለውን ለሰዎች «ኑ...» (2፡17) ብሎ ከገለጸ በኋላ ሰዎቹ መልእክቱን ተረድተውና ተነሳስተው «እንሥራ» (2፡18) እንዲሉ የሚያደርግ ነው። ከዚህ በኋላ ሸክሙና ሥራው የአንድ ሰው መሆኑ ያበቃና የማኅበሩ ይሆናል። ይህ ራእይን ከአንድ ሰው ወደ ሌሎች (ሠራተኞች) ማስተላለፍ ነው። «ኑ» ተብሎ የተጠራው ሕዝብ በአንድነት «እንሥራ» ብሎ እስኪነሳ ድረስ ማድረግ ራእይን የመግለጥ፣ የማስረዳት፣ የማስተላለፍ ትልቅ የመሪነት ችሎታ ነው።

ነህምያ ቅጥሩን የማደስ ሥራ የጀመረው ሕዝቡን በማደራጀትና የሥራ ክፍፍል በማድረግ ነው። የነህምያ አደረጃጀት በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ሥራ ፈት እንዳይኖርና ሁሉም በቅጥሩ እድሳት እንዲካፈል የሚያደርግ ድንቅ አሠራር ነው። በሥራው ታላላቆች (3፡1 22-28)፣ ካህናት (3፡17)፣ ዘበኞች (3፡29)፣ ወርቅ አንጥረኞች (3፡8 31፡32)፣ ነጋዴዎች (3፡32)፣ ባለ ሥልጣኖች መሪዎች (3፡9-12፤14፣ 16)፣ ሽቶ ቀማሚዎች (3፡8)፣ ሌሎችም ወንዶችና ሴቶች (3፡12) ሁሉ ተካፍለዋል። ጥሩ አደረጃጀት ሥራው በፍጥነት እንዲሠራና እያንዳንዱ እንደ ችሎታው (ስጦታው) እንዲያበረክት ያደርጋል። ጥሩ አደረጃጀት ብዙ ሥራን በአጭር ጊዜ ለመሥራት ያስችላል።

ነህምያ ሥራን ማቀድና ማደራጀት የሚያውቅ ታላቅ መሪ ነው። በነህምያ አደረጃጀት ቅጥሩን በማደስ ሥራ ላይ የተሠማሩት ከአርባ የማያንሱ የሥራ ቡድኖች ነበሩ። ሠራተኞችን በቡድን አደራጀ፣ የሥራ ክፍፍል አደረገ፣ በየቦታው ለሥራው የሚመጥኑ ሰዎችን





ሾመ። ሥራን ማቀድ፣ ማደራጀት፣ አፈጻጸሙን መከታተል የጠንካራ መንፈሳዊ መሪዎች ተግባር እንደሆነ ከነህምያ በግልጽ እንማራለን። ጎበዝ መሪ ሥራን የሚያቅድና አሠራርን የሚያደራጅ ነው።

የኢየሩሳሌም ቅጥር ዙሪያውን እንዲታደስ ማድረጉ የነህምያን ሌላ የማስተዋል ችሎታ ይገልጻል። ሠራተኞች የተመደቡት በቅጥሩ በሰሜን በኩል (1፡7)፣ በምዕራብ በኩል (8-13)፣ በደቡብ በኩል (14)፣ በምሥራቅ በኩል (15-32) ነበር። ሳይታደስ የቀረ፣ የተረሳ ወይም የተተወ የቅጥር ክፍል አልነበረም።

«ሁላችን ወደ ቅጥሩ እያንዳንዳችን ወደ ሥራችን» (4፡15) የሚለው የአደረጃጀትና አመራር ስልት ለአንድ ዓላማ መሰለፍን እንዲሁም የሥራ ክፍፍልን የሚመለከት የአደረጃጀት ጥበብ ነው። የበጉ በር (መሥዋዕት የሚቀርብበት) ታድሶ የጉድፍ መጣያው በር (3፡14) ግን ሳይታደስ ቢቀር ባልታደሰው በር በኩል ከውጭ የሚገባው ሁሉንም ያረክሰዋል፣ ያደባልቀዋል። ስለሆነም ነህምያ ቅጥሩ ዙሪያውን እንዲታደስ ሲያደርግ ለክፉ ነገር መግቢያ ምንም ቀዳዳ (ክፍተት) እንዳይኖር አድርጎ ቅጥሩን በሙሉ ያደሰ አስተዋይ መሪ ነው።

የዚህ ቅጥር አሠራር ምሳሌነቱ ትልቅ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ አንድ ሠራዊት አድርጎ ይቆጥራል። በሕዝቡ መካከል በአንድ ምክንያት በደል ቢኖር በዳዩ ሰው በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው፣ ማኅበሩም በዚያ ሰው በደል ምክንያት በደለኛ ይሆናል።

እዚህ ላይ የአካንን ምሳሌ (ኢያ 7፡1) መጥቀስ ይቻላል። አካን ከምርኮ የወሰደውን እርም የደበቀው በድንኳኑ ውስጥ ነው። በአካን በደል ለእስራኤላውያን መሸነፍ ሆነ (7፡5)። ስለዚህ መሪዎች የሚጠነቀቁት ዙሪያ ገቡን ነው። መሪ በእግዚአብሔር

ሥራ ውስጥ ትንሽ የሚባል ሥራ እንደሌለ የማይረሳ ነው:: ሁሉም ሰው፣ ሁሉም የአገልግሎት ክፍል እንዲቀደስ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ሥራ በጥራት እንዲሠራ ማድረግ ይገባል::

ነህምያ ሰውን በኃላፊነት ቦታ ለመመደብ የሚጠቀምበት መመዘኛ «መንፈሳዊ» ነው:: በኢየሩሳሌም ላይ አለቃ አድርጎ የሾመው ወንድሙን አናኒን በመሆኑ ጥያቄ ለሚያነሳ ሰው ነህምያ ሲያስረዳ አናኒ «ከሌሎች ይልቅ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር» (6:2) ይላል:: በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የሚሾሙ ሰዎች የሚመረጡት ለአለቃው ባላቸው ቀረቤታ፣ ባደረጉለት ውለታ ወይም ባላቸው ታማኝነት ሳይሆን በእርግጥ እግዚአብሔርን በመፍራታቸው መሆን አለበት::


ነህምያ ለሥራው ያደረገው ዝግጅት፣ ሥራውን ያደራጀበት ጥበብ አፈጻጸሙ በዛሬው ዘመን «ሳይንሳዊ» በሚባለው እቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር መለኪያ ቢነጻጸር የነህምያን ታላቅ ግንዛቤና የአመራር ጥበብ ያሳያል:: ከነህምያ ምዕራፍ 1-6 ያለውን ይህ ጸሐፊ ከእቅድ





አነዳደፍና አፈጻጸም ሂደት እንደሚከተለው አቅርቦታል::

ዕቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም
(በነህምያ መጽሐፍ ላይ የተመሠረተ ቅጥርን የማደስ ሂደት)



4. ጠንካራ መንፈሳዊ መሪ የጸሎት ሰው ነው::
በነህምያ ዘመን በኢየሩሳሌም ታላቅ ተሐድሶ እንደመጣ ይታወቃል:: ለዚህ የመጀመሪያው እርምጃ ነህምያ ለአያሌ ቀን የእግዚአብሔርን ፊት መፈለጉ፣ መጾሙና መጸለዩ ነው:: ለእግዚአብሔር ስም መከበር ቅናት ያለው መንፈሳዊ መሪ ከሁሉ በፊት ጸሎትን ያስቀድማል::
ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም መፍረስ በሰማ ጊዜ አዘነ፣ ለእግዚአብሔር ስምና ክብር ቀና:: ሀዘኑንና ስሜቱን ሁሉ ለአያሌ ቀን በጾምና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አቀረበ (1:4-10):: ነህምያ ራሱን ከአይሁድ ጋር አመሳሰለ:: አይሁድ ያሉበት ችግርና የኢየሩሳሌም መፍረስ የራሱ ችግር እንደሆነ አድርጎ ቆጠረው:: አንድ መሪ

የሚሠራው ሥራ የራሱ እንደሆነ አድርጎ እስካልወሰደው ድረስ ልቡን ለሥራው ላይሰጥ ይችላል::

ነህምያ ስለ ኢየሩሳሌም ሁኔታ ከወንድሙ በሰማበትና «ፊትህ ለምን አዘነ? ይህ የልብ ኀዘን ነው» (2:2) ብሎ ንጉሡ እርሱን በጠየቀበት ጊዜ መካከል አራት ወር ያህል ጊዜ አልፏል:: ይህ ሁሉ ጊዜ የጸሎትና የዝግጅት ነበር ማለት ይቻላል:: ወደ ንጉሡ በቀረበ ጊዜ «ምን ትለምነኛለህ?» ሲለውም ወደ አምላኩ ጸለየ (2:4)::

በመሠረቱ ጸሎት ራሱን የቻለ ትልቅ ሥራ (ተግባር) ነው:: ጸሎት ሀሳብን ሁሉ ሰብስቦ ወደ እግዚአብሔር በትሕትና መቅረብን፤ ጊዜ መመደብን፤ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር መጋደልን ይጠይቃል:: ነህምያ ከመነሻው በእግዚአብሔር ፊት ጸለየ፤ ለአያሌ ቀን ጸለየ፤ በማንኛውም ሁኔታ ከአምላኩ ጋር በጸሎት ተገናኘ::

ነህምያ ከካሴሉ ወር (ታህሳስ) እስከ ኒሳን ወር (ሚያዝያ) ለአራት ወር ያህል ጸለየ (1:1፤ 2:1) ይጾምም ነበር:: በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለሚገኙ አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ይህ ሁሉ የጸሎት ጊዜ ሥራ መፍታት ሊመስል ይችላል:: በጸሎት ያልተጀመረና በጸሎት ያልተደገፈ ተግባር ‹ሰው ሰራሽ› ብቻ ይሆናል:: የመጾም አስፈላጊነትም ራስን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ የእርሱን ሀሳብ ለመረዳት ነው:: እርሱ የሚሰበውን ለማሰብ፤ እርሱ የሚያየውን ለማየት ለመንፈሳዊ ዓይን መከፈት ነው::

ከነህምያ ሕይወት እንደምናስተውለው ለክርስቲያን መሪ ጸሎት የመጨረሻው አማራጭ ሳይሆን የመጀመሪያው ተግባራዊ እርምጃ ነው:: ጸሎት በእግዚአብሔር መታመንን ይገልጻል፤ የሥራ ራእይንና የአሠራር ጥበብን ያስገኛል:: ጸሎት በኃያሉ እግዚአብሔር ሥር በትሕትና ራስን ዝቅ ማድረግ በመሆኑ በራሱ ማስተዋል የሚደገፍና ትዕቢተኛ ሰው አይጸልይም:: የሚጸልይ ሰው ጸሎትን





በሚሰማው በእግዚአብሔር ታምኖ ስለሚሠራ በተግባሩ ብርቱ ነው::

## 5. ጠንካራ መንፈሳዊ መሪ የተግባር ሰው ነው::

ከጸሎቱ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር በልቡ ያደረገውን ይዞ የተግባር እንቅስቃሴ አደረገ:: ጸሎቱንም ወደ ተግባር መተርጎም ጀመረ:: ራእዩን ወደ ተግባር ለመተርጎም የሚያስፈልገውን መሰናዶ አደረገ (2:5-8)፤ ዓላማውን ለሕዝቡ አስረዳ፤ የእድሳቱን ሥራ ጀመረ::

ነህምያ ንስሐ የሚገባ፤ የሚማልድ፤ የሚያለቅስ፤ የጸሎት ሰው ነው:: ጸሎት ኃይል እንዳለው ለውጥም እንደሚያመጣ የሚያምን መሪ ነው:: ስለዚህ ከመነሻው አንስቶ በማያቋርጥ ጸሎት የጸና መሪ ነው:: ነህምያ የተግባርም ሰው ነው:: ያደራጃል፤ ከሕዝቡ ጋር አብሮ ቅጥሩን ይሠራል፤ የኢየሩሳሌም በሮች በምሽት እንዲዘጉ (13:19)፤ በሮቹም እንዲጠበቁ አድርጓል (13:19-22):: እየሠራም ይጸልያል::

ከእግዚአብሔር ጋር ከፍት የሆነ የግንኙነት መስመር የነበረው፤ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የሚጸልይ እንዲሁም ተግቶ ሥራውን የሚሠራ ነው:: ከዚህም የተነሣ ለረጅም ዘመን ፈርሶ የኖረን ቅጥር በ52 ቀን እንዲጠናቀቅ ያደረገ ታላቅ መሪ ነው::

መሪዎች የሚጸልዩ መሆን አለባቸው:: ራእይ ለመቀበል፤ ምሪትን ለማግኘት፤ ለሚነሣው ችግር ጥበብ ለመቀበል የእግዚአብሔርን ፊት የሚፈልጉ መሆን አለባቸው:: እንዲሁም መሪዎች በሥራው በትጋት የሚሳተፉ፤ አሠራሩን በቅርበት የሚከታተሉ፤ የሚገመግሙ መሆን ይገባቸዋል:፤ መሪ የሚጸልይ ደግሞም የሚሠራ ነው::

ስለዚህ በጸሎት መትጋት የሚያስፈልገውን ያህል ትጉህ ሠራተኛ ሆኖ መገኘትም ከእግዚአብሔር አገልጋይ የሚጠበቅ ዓይነተኛ ባሕርይ ነው:: ነህምያ በሥራ ይበረታል፤ በጸሎት ይተጋል (1፡4 11፤ 2፡4፤ 13-14፤22፤29፤31):: ጸሎትና ተግባር የተያያዙ ናቸው:: የነህምያ የመሪነት ቀመር (ፎርሙላ)፡- ጸሎት-ራእይ-ጸሎት-ተግባር-ጸሎት-ተግባር-ጸሎት... ነበር ማለት ይቻላል::

## 6. መንፈሳዊ መሪ በመልካሚቱ የአምላኩ እጅ ይታመናል::

ነህምያ ከንጉሡ ፈቃድ አግኝቶ ወደ ኢየሩሳሌም ስለመሄዱ ሲናገር «ንጉሡም በእኔ ላይ መልካም እንደ ሆነችው እንደ አምላኬ እጅ ሰጠኝ» (2፡8) አለ:: ንጉሡ ፈቃድ የሰጠው መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ በነህምያ ላይ ስለነበረች ነው:: እንዲሁም «የአምላኬም እጅ በእኔ ላይ መልካም እንደሆነች፥ ንጉሡም የነገረኝን ቃል ነገርኋቸው። እነርሱም እንነሣና እንሥራ አሉ። እጃቸውንም ለበጎ ሥራ አበረቱ» (2፡18) አለ።

የእግዚአብሔር እጅ በሰው ላይ በመልካምነት ስትገለጥ ከንጉሥ ፈቃድ፤ ምሕረትና ሞገስ (2፡28፤ ዳን 1፡9፤ ሐዋ 7፡10) ታስገኛለች:: ምክንያቱም «የንጉሥ ልብ እንደ ውኃ ፈሳሾች በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ ወደ ወደደውም ያዘነብለዋል» (ምሳ 21፡1)።

እግዚአብሔርን ለሚፈሩት መልካሚቱ እጁ ትታወቃለች:: እስራኤልን ከባርነት ነጻ ያወጣች፤ ባሕሩን ያደረቀችና በደረቅ ምድር ያሻገረች (ዘጸ 6፡1፤6፤ 1ነገ 8፡42፤ ኤር 32፡21)፤ ሕዝቡ በንስሐ ወደ እርሱ እንዲመለሱ አንድ ልብ የሰጠች ናት (2ዜና 30፡12):: ለሚቃወሙት ደግሞ በቁጣ ስትገለጥ ጠላትን የምታደቅ ብርቱ እጅ ናት (ዘጸ 13፡9፤14፤ 15፡6፤ ኢሳ 66፡14):: እሳዳጆችን





በባሕር የጣለች፤ ታላላቅ ነገሥታትን የመታች ናት (መዝ 136፡12-18፤ ኢሳ 51፡9-10)::

ለነህምያ በንጉሡ ፊት ምሕረት፤ በመንገዱ ሁሉና በቅጥሩ ሥራ መከናወን የሰጠችው መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ (1፡11) የፈረሰውን ለማደስና በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ለሚነሳሡ ሁሉ በመንገድ ላይ ጥበቃ፤ በሥራው መከናወን፤ ጥንካሬ፤ ብርታት ትሰጣለች (እዝ 7፡9፤27):: እንዲሁም መንፈሳዊ መሪዎች ሙሴን፤ ነህምያንና ሌሎችንም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ባገዘችና ባጸናች መልካሚቱ የእግዚአብሔር እጅ የሚደገፉ ሊሆኑ ይገባል::

## 7. መንፈሳዊ መሪ በምሳሌነት የሚመራ አገልጋይ-መሪ ነው::

ነህምያ የአገልጋይ መሪ ምሳሌ ነው:: መሪ የሚጸልይ፤ የሚያቅድ፤ ሥራን የሚያደራጅ ብቻ ሳይሆን ያወጣውን እቅድ ከሠራተኞቹ ጋር አብሮ የሚሠራም ነው::

በመሪነት ላይ ያለ ሰው የሥራ መመሪያ (ትእዛዝ) የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ባዘጋጀው እቅድ ውስጥ ያለ የትኛውንም የሥራ ዓይነት እንደ ሌላው የእግዚአብሔር ሕዝብ በአቅሙ በሚቻለው ሁሉ አብሮ ለመሥራት የሚወድ ሰው መሆን አለበት:: ለቅጥሩ ሥራ እስከሆነና አስፈላጊ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ለምሳሌ ድንጋይ መጥረብና መሸከም መደርደርም ቢሆን እንደ ሌላው ሰው የአቅሙን ለማድረግ የተዘጋጀ ሊሆን ያስፈልጋል:: መሪ ሥራንና አሠራርን በመሥራት የሚያሳይ ነው::

መሪዎች በአድካሚ ሥራ ከሕዝቡ ጋር አብረው የሚሠሩ እንጂ እጃቸው እንዳይቆሸሽ ከሥራ የሚርቁ አይደሉም:: ነህምያ «ኑና

የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ» (2:17)፤ «ሁላችንም ወደ ቅጥሩ እያንዳንዳችንም ወደ ሥራችን» (4:15)፤ «ሥራውንም ሠራን» (4:21)፤ «እኔና ወንድሞቼም ...ልብሳችንን አናወልቅም ነበር» (4:23)፤ «አጥብቄ የቅጥሩን ሥራ ሠራሁ» (5:16) ሲል በእድሳቱ ሥራ ላይ በመሰጠት መሰለፉን ያስገነዝበናል:: ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ «ከሁላቸው ይልቅ ...ደከምሁ»[19] (1ቆሮ 15:10) እንዳለው ነው::

ነህምያ ከሠራተኞቹ ጋር አብሮ የሚሠራና በሥራ ቦታው የሚገኝ ሰው ስለነበረ በሥራው ላይ ችግር ሲነሣ ሕዝቡን ያበረታታል፤ ለአሠራሩም እንደ አስፈላጊነቱ ወዲያውኑ ተለዋጭ የአሠራር ስልት ያዘጋጃል:: ንቁ መሪ በችግር ጊዜ ሥራው ሳይቋረጥ ወደዋናው ግብ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ይፈልጋል::

ነህምያ እግዚአብሔርን በመፍራቱ (5:15)የሚገባውን እንኳን ሳይጠይቅ (5:14) በቅንነት ያስተዳደረ ሰው ነበር:: ምክንያቱም «አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ከብዶ ነበርና ለአለቃ የሚገባውን ስንቅ አልሻም ነበር» (5:18) አለ:: የአለቅነት ቦታ የሚፈለገው ለራስ ክብርና ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ገዢነት ነው:: መንፈሳዊ መሪነት ገዥነት አለመሆኑን ነህምያ በሕይወቱ ያሳየ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ነው:: ሕይወቱ «ሠርቶ ማሳያ» ነበር:: እግዚአብሔርን የሚፈሩ መሪዎች በሕዝቡ ላይ ቀንበርን አያከብዱም::

በመንፈሳዊ አመራር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ የሕይወት ለውጥ የሚመጣው መሪዎች ራሳቸው እግዚአብሔርን በመፍራት ሲኖሩ ነው:: መሪዎች በሥራ በመትጋት ምሳሌ መሆን እንዳለባቸው ሁሉ እግዚአብሔርንም በመፍራት ለሕዝቡ ምሳሌ እንዲሆኑም ይጠበቃል::

[19] በአዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ:- «ከሁሉም በላይ በትጋት ሠርቻለሁ» ይላል::





በአጠቃላይ መልካም መሪዎች ለሕዝቡ ራእይን የሚያካፍሉ ሥራን የሚሰጡ ብቻ ሳይሆኑ በሥራውም ውስጥ ገብተው «እጃቸው እስኪቆሸሽ» የሚሠሩ ናቸው:: መሪዎች በሥራ ታታሪ ሲሆኑና በምሳሌነት ሲመሩ ከፍተኛ ውጤት ይገኛል::

## 8. መንፈሳዊ መሪ በሥራው ላይ ለሚነሱ ችግሮች ‹እጁን የማይሰጥ› ነው::

የነህምያ መሪነት ከመነሻው ጀምሮ ተቃዋሚዎች የበዙበት ነበር:: ሥራው እየቀጠለ ሲሄድ ተቃውሞው እየበረታ ቢሄድም እርሱ ግን በብዙ ጸሎት፤ ትዕግሥትና ማስተዋል፤ እንዲሁም ችግሮቹን እንደ አመጣጣቸው በንቃት በማስተናገድ በድል ጨረሰው::

በነህምያ ላይ በጠላትነት የተነሱት ሰዎች ዋና ምክንያታቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደተዋረደ እንዲቆይ የሚፈልጉና የኢየሩሳሌም ቅጥር መሠራት፤ የእግዚአብሔርም ቤት መታደስ ቅር የሚያሰኛቸው ናቸው:: እንዲሁም ዋና ጠላት ሆነው የተነሱት ጦብያ በአሞናውያን ዘንድ ሰንበላጥም በሰማርያ አለቆች እንደ ነበሩ ስለሚታሰብ አንድ ከምርኮ የተመለሰ ሰው በአንድ ጊዜ በኢየሩሳሌም ታላቅ ለውጥ ማምጣት መቻሉ ሳያስቀናቸው አልቀረም:: ይህ ሰው ነህምያ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕዝቡን ልብ አግኝቶ ለታላቅ ሥራ ማሰልፍ መቻሉ ሌላ የቅንዓት ምክንያት ይሆናል:: ስለሆነም የተጠቀሙበት የተቃውሞና የክስ መስመር የነህምያን ማንነት የሚያብጠለጥልና የንጉሡንም ቁጣ የሚያነሳሳ ነበር::

እዚህ ላይ የምናስተውለው ነገር የችግሮቹ ዓይነትና አመጣጥ የተለያየ ቢሆንም ችግሮቹ እንዲያስገኙ የተፈለገው ውጤት አንድ መሆኑን ነው፤ ይህም ሥራውን ማስተጓጎልና ማስቀረት:: ነህምያ እያንዳንዱን ችግር ያስተናገደበትን ሁኔታና የሰጠውን መፍትሔ

ስናጤን ደግሞ የምናስተውለው ነገር ለየችግሩ የሚሰጠው ምላሽ እንደየችግሩ እንደሚለያይ እንጂ አንድ ወጥ አለመሆኑን ነው፡፡

በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የሚነሱ ጠላቶች ከውጭ የሆኑ (ከማያምኑት ወገን) ብቻ አይደለም፡፡ ከውስጥ ካሉትም መካካል ድንገት የሚንሸራተቱ፤ ወይም የሚከዱ፤ እንደ ይሁዳ አሳልፈው የሚሰጡ (መዝ 41፡9 ዮሐ 13፡18)፤ ሐሰተኛ ትንቢት የሚናገሩም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ለክርስቲያን መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የከረረው ተቃውሞ የሚመጣው በውስጥ ካሉ ወንድሞች ከሚባሉ ሐሰተኛ ወንድሞች ሊሆን ይችላል፡፡

በውጭ ያለው የጠላት ተቃውሞ ባየለበት ሰዓት የውስጥ ችግር ደግሞ ብቅ አለ፡፡ አንዱ ችግር መሰላቸት ነበር፡፡ የውስጥ መሰላቸት የጀመረው የግንቡ እድሳት ግማሹ ካለቀ በኋላ በመሆኑ ፍርስራሹ በግማሽ እንደሚቀንስ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ችግሩ ከሥራው ብዛት ይልቅ የመንፈስ መዛል ነበር፡፡

ሌላው የውስጥ ችግር እግዚአብሔርን ካለመፍራት የተነሣ በአይሁድ መካከል የኖረ የውስጥ በደል ነው፡፡ አገዛዝ በሕዝቡ ላይ ከብዶ ነበር (5፡18)፡፡ እህል ከመበደርና ከወለድ ክፍያ ጋር በተያያዘ ሕዝቡ እጅግ ተጎሳቁሎ ነበር፡፡ ይህ ለቅጥሩ እድሳት ሌላ እንቅፋት ሆነ፡፡ ነህምያ ግን ሕዝቡን ሰብስቦ አነጋገረ፤ ወለድ እንዲቆም አደረገ፤ የከበደውንም አገዛዝ አቃለለ፡፡
ነህምያን ለመግደልም በውጭ ያሉ ጠላቶች በውስጥ ካሉ ወዳጆቻቸው ጋር በመመሳጠር የሚደርጓቸው ቅንብሮች ነበሩ፡፡ በአምላኩ የሚታመን ደፋር ነህምያ በሚነሣው ችግር ሁሉ እምነቱን በአምላኩ ላይ ያደረገ ነው «አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል» (4፡19) እያለ ሕዝቡን ያደፋፈረ መሪ ነው፡፡





ችግርን ለማሸነፍ በሰው ደረጃ ሁልጊዜ ዝግጅት ማድረግ የሚያስፈልግ ቢሆንም በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የሚነሣ ተቃውሞ ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር ስም ላይ እንደተነሣ ማስተዋል ይጠቅማል፡፡ እግዚአብሔር ለስሙ ቀናተኛ ስለሆነ ሰልፉ የእግዚአብሔር ነው፡፡

እንግዲህ ውጤታማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር ችግርና ተቃውሞ በበዛበት ሁኔታ ይበልጥ በእግዚአብሔር በመደገፍ ከእርሱ ጥበብናን ድፍረትን በመጠየቅ መምራት ነው፡፡ በመንፈሳዊ አመራር የራስ እውቀት (ጥበብ) እንዲሁም ድፍረት (ወኔ) ብዙ እርምጃ አያራምድም፡፡ ጠላት ያዘጋጀውን ወጥመድ ለማለፍ፤ ከጠላት ጥበብ በላይ የሆነ ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሰጠው ጥበብ ነው፡፡

## 9. መንፈሳዊ መሪ የእግዚአብሔርን ቃል የተሐድሶ ዋና መለኪያ የሚያደርግ ነው፡፡

እውነተኛ ተሐድሶና መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) የሚኖረው ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በትክክል ሲረዳ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሀሳብ ደግሞ በግልጽ የሚታወቀው በቃሉ በኩል ነው፡፡ መንፈሳዊ ተሐድሶ ወደ እግዚአብሔር ሀሳብ መመለስ በመሆኑ ያለ ቃሉ ሀሳቡን መረዳት ሊኖር አይችልም፡፡ መንፈስ ቅዱስ የተጻፈውን ቃሉን በማብራት በጊዜው ምን መደረግ እንደሚገባው ይገልጻል፡፡ መለኪያው ቃሉ ነው፡፡

በነህምያ ዘመን ቅጥሩ ከታደሰ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነበር፡፡ ሕዝቡ ከተሰበሰበ በኋላ «ካህኑ ዕዝራ ሕጉን ...አነበበው ...የሕዝቡም ሁሉ ጆሮ የሕጉን መጽሐፍ ለመስማት ያደምጥ ነበር» (2-3)፡፡ «ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፤ ሕዝቡም

የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር» (8:8):: እንዲህ ዓይነቱ ቃሉን የማስተዋል ሂደት ሕዝቡን በእንባ ወደ ተገለጸ ንስሐ መራው::

ለሰው ሕይወት ትክክለኛው ሚዛን ቃሉ በመሆኑ የሕይወት ተሐድሶ በቃሉ መነበብ ጀመረ:: ሰው ትክክለኛውን ሲያውቅ ምን ያህል እንደሳተ (ከመሥመር እንደ ወጣ) ማየት ይጀምራል:: የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ በመሆኑ ነፍስና መንፈስን እስኪለይ ድረስ ይወጋል (ዕብ 4:12):: ስለዚህ ለመንፈሳዊ ተሐድሶ የእግዚአብሔር ቃል ማዕከላዊ ነው:: ተሐድሶ ያለ እግዚአብሔር ቃል አይሆንም::

## 10. መንፈሳዊ መሪ የተሐድሶ ዋናው ግብ ንጹህ አምልኮን መመለስ እንደሆነ የሚያውቅ ነው::

ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌም ቅጥር በማደስ የተቀደሰው ሥፍራ ከርኩስ ነገር ጋር እንዳይደባለቅ አደረገ:: ይህ በአካል የሚታይ ግንቡን እንደገና በመሥራት የተገኘ መታደስ ነው:: ቅጥሩ በመታደስ ላይ እያለም በሕዝቡ መካከል ትልቅ የፍትሕ ችግር እንደነበረ ስለ ተገነዘበ በሕዝቡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትም ማስተካከልን አደረገ፤ ተሐድሶን አመጣ:: ድሆች ቀንበር እንዲቀልላቸው ከአበዳሪዎችና አለቆች ጋር ስለ እነርሱ ተሟገተ::

የፈረሰን ቅጥር ማደስ የእግዚአብሔር ሀሳብ ያለበት አንድ መልካም ነገር ነው:: ይህ በአሁኑ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን ህንፃ እንደ መሥራት ሊሆን ይችላል:: የማደስ ተግባር ግን እዚህ ላይ ማብቃት የለበትም፤ በራሱ ብቻውን ግብ ሊሆን አይችልምና:: ቅጥርን ማደስ በራሱ ግብ ሆኖ እዚያ ላይ ቢያበቃ ዋናውን ተልዕኮ መዘንጋት ይሆናል::





ከቅጥሩ መታደስ ባሻገር የእግዚአብሔር ሕዝብ ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት በማስተካከል፤ ንጹህ የሆነ ሕይወት በመኖር እርሱን ሊያመልክና ቃል ኪዳኑን ሊጠብቅ ይገባል:: የውጭው ቅጥር መታደስ መልካም ሲሆን እጅግ መልካሙ ግን የሕይወት መታደስ ነው:: ስለዚህ ነህምያ ቅጥር ካደሰ በኋላ ወደ ሰዎቹ ሕይወት ተመለሰ::

የእግዚአብሔር ቃል በካህኑ ዕዝራ ሲነበብ ሕዝቡ የረሳውን አስታወሰ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳኑን አደሰ (10:1-29):: የተሐድሶ ግብ እያንዳንዱ ሰው በግል፤ ማኅበሩም በአንድነት ወደ እግዚአብሔር መመለሱና ንጽህ አምልኮን ማቅረቡ ነው::

እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት ስላዘነ ሕዝቡን ለመበተን፤ ኢየሩሳሌምንም ለመፍረስ አሳልፎ ሰጥቶአል:: ሕዝቡ ወደ ቀደመው ቃል ኪዳን ሲመለስ ዕዝራ ሕዝቡን «የእግዚብሔር ደስታ ኃይላችሁ ነውና» (8:10) እንዳላቸው እግዚአብሔር ደስ ይለዋል:: እርሱ ደስ ሲለው ለሕዝቡ በረከት፤ ጉልበት ይሆንለታል:: የእግዚአብሔር መቆጣት በቃል ኪዳን ሕዝቡ ላይ መበተንን፣ መከራን፣ በጠላቶቹም ፊት መሸነፍን እንደሚያስከትልበት ሁሉ ደስታው ደግሞ ሰላምን፤ እረፍትን፤ ተዘልሎ መኖርን፤ ኃይልን ያመጣለታል::

የአንድ መሪ ትልቁ ተልኮው እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ ይለው ዘንድ እንደ ነህምያ ሕዝቡን ወደ ንስሐ መምራት ነው:: ስለሆነም የመንፈሳዊ መሪ ዋናው ትኩረት ከሕንጻ ሥራ በላይ ነው:: ትኩረቱ የሕዝቡ ሕይወት መታደሱና መታነጹ፤ እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘቱ እስከሚታወቅ ድረስ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲመጣ መትጋቱ ነው::

## ll. መሪ ውጪውን በማደስ ብቻ የማያቆም፤ ውስጡንም ከተደባለቀና ከእንግዳ ነገር የሚያነጻ ነው::

ነህምያ ከሱሳ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ቆይቷል (5:16):: ተመልሶም በመሄድ ጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ እንደገና ከሱሳ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (13:6-7):: ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ በኢየሩሳሌም ውስጥ ያገኛቸው ነገሮች እርሱ የጠበቀው ዓይነት አልነበሩም:: አሁንም ለሌላ ማጽዳት ሥራ ተነሣ::

የኢየሩሳሌም ቅጥር እንዳይታደስ አጥብቆ የተቃወመው ጦቢያ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ለመግባት ከማይፈቀድለት ወገን ሆኖ እያለ (13:1፤ ዘዳ 2:3-4)፤ ከቀሳውስቱ ጋር በጋብቻ ተዛምዶ ነበርና (6:17-19፤ 13:4-5) በቤተ መቅደሱ ጓዳ (ከፍል) ይቀመጥ ነበር (13:4-5):: ካህናቱና መዘምራኑ ተበትነው (13:10) አገልግሎታቸውም ተጓጉሎ ነበር:: በቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮና ንግድ አብሮ ይካሄድ ነበር (13:15-18):: በሕዝቡ መካከል «የሰሎሞን ኃጢአት» (13:23) ወይም የተደባለቀ ጋብቻ ተንሰራፍቶ ነበር:: እንዲህ ዓይነት እንግዳ የሆኑ ነገሮች በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሕይወቱ ከፍል መሆን ጀምረው ነበር::

ነህምያ እንደ ተመለሰ ሕዝቡን እና የእግዚአብሔርን ቤት እንዲህ ከመሰለ ኃጢአት ለማጽዳት በድፍረት ተነሣ:: ይህንም ሲያደርግ የጦብያን ንብረት ከታላቁ ጓዳ አውጥቶ ጣለ (13:8)፤ ከፍሎቹ እንዲጸዱ አዘዘ (13:9):: ይህ ድርጊት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ካደረገው ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ልብ ማለት ያስፈልጋል (ዮሐ 2:16):: ቤተ መቅደሶቹ ከጸዱ በኋላ የተበተኑት ካህናቱና ሌዋውያኑ እንዲመለሱ፤ የመቅደስ አገልግሎቱና የአምልኮ ሥርዓት እንደገና እንዲጀመር (13:12) አደረገ:: ሰንበትን ስላለማክበራቸው ታላላቆቹንና አለቆቹን ገሰጻቸው፤ ነጋዴዎቹንም አስጠነቀቃቸው (13:7፤20-21)፤ በሰንበት





በሮቹ እንዲዘጉ አዘዘ:: ተግባራዊነቱንም በቅርቡ ተከታተለ (13:9)፤ ታማኝ ሰዎችን ለአገልግሎት መረጠ (13:13):: የተደባለቀ ጋብቻን ተቃወመ፤ ከለከለ (13:23-27):: እንዲሁም የክህነቱን ሥርዓት ያላከበረውን የካህኑን ልጅ ቀጣው (13:28-29)::

እንግዳ ነፉር ወደ እግዚአብሔር ቤት ማስገባት ከዓለም ጋር መወዳጀት ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቤት «እንግዳ ነገር» የሚገባው በአመራር ወይም ከፍ ባለ አገልግሎት ቦታ ላይ ባሉ ሽማግሌዎች፤ እረኞች፤ ቄሶችና አስተማሪዎች በኩል ሲሆን ይታያል:: በነህምያ ዘመን እንግዳ ነገርን ወደ ቤተ መቅደስ ያስገባው ሊቀ ካህኑ ኤልያሴብ ነበር:: ኤልያሴብ ቅጥር በማደስ ቀዳሚ ሰው ነበር (3:1):: ሆኖም ቆይቶ ኤልያሴብ ከጦብያ ጋር ተወዳጀ (13:4)፤ ለጦብያም ጓዳውን አዘጋጀ (13:7) ተብሎበታል::

ጦብያ ያገባው የኤራን ልጅ ነበር (6:17):: ኤራ ከዘሩባቤል ጋር የመጣ ዕብራዊ ነው (ዕዝ 2:5):: የጦቢያ ልጅ ያገባው የሜሱላምን ሴት ልጅ ነው (6:17)፤ ሜሱላም በቅጥሩ ሥራ በግንባር ቀደምትነት የተሳተፈ ሰው ነበር (3:4):: የሊቀ ካህኑ የኤልያሴብ ልጅ ደግሞ የሰንባላጥ አማች ነበር (13:18)::

በዚህም ዘመን ቢሆን ክርስቲያን መሪዎች በተለያየ መልክና ቅርጽ ከዓለማውያን ጋር በመወዳጀት ዓለማዊ የሆነ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲገባ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ሊቀ ካህኑ ኤልያሴብና ሜሱላም ቅጥር በማደስ ቀዳሚ ሰዎች ነበሩ (3:1፤4):: የእግዚአብሔርን ቤት ቅጥሩን ቢሠሩም የውስጥ ሕይወታቸው ግን ፈርሶ ነበር:: እነዚህ የአስመሳይ አገልጋዮች ምሳሌ ይሆናሉ:: አስመሳይ አገልጋዮች በውጭው ሥራ ላይ የሚበረቱ በውስጥ ሕይወታቸው (በቤተ ሰባቸው፤ ትዳራቸው፤ በአመራራቸው) በኃጢአት የፈረሰ ሕይወት ያላቸው ናቸው::

እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች አንዱ መታወቂያቸው እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ስለማይፈሩ እነጦቢያን ከማስወጣት እነኤልያሴብን ከመገሰጽ አይመለሱም:: የእግዚአብሔር ቤት ጓዳ ለጠላት ዓላማ ሲውል፤ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንግዳ ነገር ሲገባ የማይቆጣ መሪ፤ ክርስቲያናዊ መሪ አይደለም::

ነህምያ በመሪነት በቆየ መጠን ለጽድቅ ያለው ጥንካሬ አልቀነሰም:: የእግዚአብሔርን ቤት ከእንግዳ ነገር ለማንጻት የነበረው ቁርጠኝነት እየጨመረ ሄደ:: መጨረሻን ማሳመር!!

በአጠቃላይ ነህምያ የእግዚአብሔር ቤት ከውጭም ከውስጥም ከሁሉም አቅጣጫ የተጠበቀ እንዲሆን የተጋ መሪ ነው:: ይህን ሲያደርግ ካህናት ቢሆኑ አለቆች፤ ሀብታም ነጋዴዎች ቢሆኑ ሌላ ሰው ማንንም አልፈራም:: እርሱ የሚፈራው ሕያው እግዚአብሔርን ብቻ ነበር::

12. ታላቅ መሪ የተከናወነው መልካም ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር እንደ ተሠራ የሚያውቅ ነው::

ነህምያ የፈረሰና የተቃጠለን ቅጥር በብዙ ጠላቶች መካከል ከፍርስራሹ አንስቶ ወደ ቀደመው ደረጃ ያመጣ መሪ ነው:: ማንም «መሪ» ተብሎ የሚጠራ ሁሉ ሊያደረገው የማይችለውን ታላቅ ሥራ ሠርቷል:: ነህምያ «ልዩ» መሪ ነው:: ስለዚህ ነህምያ ስለ ችሎታውና ስለተገኘው ውጤት አስቦ ለስሙ «ሐውልት» ቢያስተክል አያንስበትም::

አመራር ራእይን ለሕዝብ በመግለጽ ከራእዩ በኋላ ማሰለፍን፤ ሥራን ማቀድን፤ ማደራጀትን፤ መከታተልን፤ በጠላቶች ፊት ድፍረትን ይጠይቃል:: ነህምያ በዚህ ሁሉና ሥራው እጅግ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲያልቅ በማድረጉ «የተዋጣለት» መሪ ነበር::





እንዲሁም እግዚአብሔርን ይፈራል፤ የተደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተደረገ ያውቃል:: ነህምያ ብዙ ዋጋ ቢከፍልም ብድራቱን ከእግዚአብሔር ይጠብቅ ነበር እንጂ ከሰው ለማግኘት አልሞከረም::

ነህምያ በሥራው ላይ የእግዚአብሔርን ድርሻ ያውቃል:: ስለዚህ በእርሱ ታመነ (4:4-5):: እግዚአብሔር ራእይን (2:12፤ 7:5)፤ በአለቆችና በነገሥታት ፊት ሞገስን የሚሰጥ (2:8)፤ በእያንዳንዱ የሥራ ደረጃ መሪ እንደሆነ ያውቃል:: በችግርም ጊዜ «አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል» (4:20) ብሎ በእርሱ ይታመናል:: ከሆነውም ነገር የተነሣ ጠላቶቻቸው «ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደተደረገ አወቁ» (6:16)::

በአጠቃላይ ለብዙ ዓመታት ፈርሶ የኖረ ዙሪያው 7.2 ኪ.ሜ ያህል የሚሆነው ቅጥር በ52 ቀን ውስጥ መታደሱ ለጠላቶችም እንኳን የማይታመን ሥራ ሆኖባቸዋል:: ትሑት የሆነውም ነህምያ የተደረገው መልካም ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተደረገ ተናገረ:: መንፈሳዊ መሪ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን ባለመዘንጋት ሁልጊዜ ክብርን ለአምላኩ ይሰጣል::

በማጠቃለል:- የነህምያ ሁኔታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» (ሉቃ 12:34) ያለውን ቃል ያሳስበናል:: ነህምያ በሱሳ እየኖረ ልቡ ኢየሩሳሌም ነበር::

ነህምያ የኢየሩሳሌምን የፈረሰ ቅጥር የሠራ፤ አለቆች በድሆች ላይ ያደርሱት የነበረውን በደል ያስቀረ፤ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳኑን እንዲያድስ ያነሳሳ፤ ቤተ መቅደሱንና አገልጋዮችን ከእንግዳ ነገር ያጸዳ ታላቅ መንፈሳዊ መሪ ነው:: የቅጥሩ መታደስ የመጀመሪያ ደረጃ ነው፤ ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳኑን

ማደሱና ከእንግዳ ነገር መጽዳቱ ደግሞ ከፍ ያለው ደረጃ ነው:: የነህምያ የመሪነት ትኩረት የእግዚአብሔር ስም ይከበር ዘንድ የፈረሰው እንዲታደስ፣ ሕዝቡ ከበደላቸው በንስሐ እንዲመለሱና የተደባለቀው እንዲጠራ ማድረግ ነው::

ለትልቅ መንፈሳዊ ሥራ ትልቅ ጠላት እንዳለው የሚያውቅ እንደ ነህምያ ዓይነት መሪ በጠላቶቹ ማባበል አይደለልም፣ ዛቻቸውንም አይፈራም፣ ይልቁን በአምላኩ በመታመን በትጋት ሠርቶ ይጨርሳል:: እንዲህ ያለ መሪ «ተጀምሮ በእንጥልጥል የቀረ ሥራ ያልተጀመረ ያህል ነው» ብሎ ስለሚያስብ በአምላኩ ታምኖ የጀመረውን ለመጨረስ ይተጋል::

ነህምያን ከሥራው ለማዘናጋት ‹ና እንገናኝ› ላሉት ሁሉ «…ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፤ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም፣ ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል?» (6:1-4) በማለት መለሰላቸው:: በእግዚአብሔር ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው ከሥራው የሚያዘናጋውንና የሚገዳደረውን ሁሉ በእግዚአብሔር ታምኖ በማስወገድ የተሰጠውን ኃላፊነት ዳር ማድረስ ይጠበቅበታል:: ዓይኑን በችግሩ ላይ የሚያደርግ ሰው የተጠናቀቀ ቅጥር ማሰብ አይችልም:: የእግዚአብሔርን ትልቅነት የሚያስብ ግን ችግሩ ስለሚያንስበት በርትቶ ይሠራል::





## ምዕራፍ 6

# ጴጥሮስ

ስምዖን ይባል የነበረው ጴጥሮስ የዮና ልጅ ነው (ማቴ 16:17፤ ዮሐ 1:42):: እንድርያስ የሚባል ወንድም ነበረው (ማር 1:16):: በገሊላ ባሕር አጠገብ በሚገኘው ቅፍርናሆም ዓሣ አጥማጅ ነበር (ማር 1:21፤29):: ታንኳም ነበረው (ሉቃ 5:3):: ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ወንድሙን እንድርያስን ዓሣ ሲያጠምዱ አግኝቷቸው ከኋላው እንዲከተሉትና ሰዎችን እንዲያጠምዱ ጠራቸው (ማቴ 4:18-19፤ ማር 1:16-17)::

ጌታ ኢየሱስ ስምዖንን ሲያገኘው ‹ኬፋ› አለው (ዮሐ 1:42):: ኬፋ የአረማይስጥ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ዓለት ማለት ነው:: ‹ኬፋ› በግሪክኛ ጴጥሮስ ማለት ሲሆን ትርጉሙም ዓለት ማለት ነው:: ወንድማማቹ እንድርያስና ጴጥሮስ ከአስራ ሁለቱ የጌታ ደቀ መዛሙርት መካከል ነበሩ:: ጴጥሮስ ደግሞ ጌታ በጣም ካቀረባቸው ሦስት ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ነበር:: ጴጥሮስ ያገባ ሰው ነበር (ማቴ 8:14-15፤ ማር 1:29-31፤ ሉቃ 4:38፤ 1ቆሮ 9:5):: እንደ ፈሪሳውያን የአይሁድ ሕግን የተማረ ሰው አልነበረም (ሐዋ 4:13)::

በወንጌሎች እንደምንመለከተው ከደቀ መዛሙርት መካከል አብዛኛውን ጊዜ ስሙ ቀድሞ የሚጠራው የጴጥሮስ ነው:: ከአኩያሞች መካከል ቀዳሚ እንደ ማለት ነው:: እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ቀድሞ የሚናገር በመሆኑ ‹አፈ